ነሐሴ 2014
ቅጽ ፪ ቁጥር ፪

# ንስንስ

ትኩረቷን በLBTQ ላይ አድርጋ በየሩብ ዓመቱ የምትታተም መጽሔት

Nisnis - quarterly magazine focusing on LBTQ issues



# የመረጥናቸው ቤተሰቦች

አታሚ/Publisher
QUEER ETHIOPIA
ኩዊር ኢትዮጵያ




# የራስዎን ድምፅ ያድምጡ

www.soundcloud.com/ethioqueer

# ንስንስ

ቅጽ ፩ ቁጥር ፩

በየሩብ ዓመቱ የምትታተመው ንስንስ
በኢትዮጵያ እና በዳያስፖራ የሚገኙ LBTQ
ጉዳዮች ላይ የምታተኩር መጽሄት ናት።

ለጥያቄዎች :
etqueerfamily@gmail.com

በኲዊር ኢትዮጵያ የታተመ
አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
© ነሐሴ 2014

## ማውጫ

3 የአርታዒያን መልዕክት

4 ቤተሰቦቻችንን መምረጥ

11 መጀመሪያ ኲዊር ኢትዮጵያዊ ስትተዋወቁ እንዴት ነበር?

12 ማህበረሰቦችን መገንባት፡ የቀድሞ ፍቅረኞች እንደ ጓደኞች

15 መጀመሪያ ኲዊር ኢትዮጵያዊ ስትተዋወቁ እንዴት ነበር? (የቀጠለ)

16 የጓደኝነት ፖለቲካ

19 በማህበራዊ ገጾች ላይ ቤትን ማግኘት

21 በአጋሮቻችን ውስጥ ማህበረሰቦችን ማፍራት

24 ለኛ ብቻ የሆነ ቦታ : በዐልን ከመረጥነው ቤተሰብ ጋር አብሮ ከማክበር የሚገኘው ደስታ

27 ከማንነት በላይ፡ እሴቶቻችንን ማመጣጠን

29 የስጋ ቤተሰብ = የመረጥነው ቤተሰብ

32 አስደሳች ነጸብራቅ፡ የ20 አመት ጓደኝነት

35 የተመረጡ ቤተሰቦች - ኲዊር ጓደኝነቶች እና ማህበረሰቦች አስፈላጊ ናቸው ብለው ያስባሉ?



# QUEER ETHIOPIA

# ኩዊር ኢትዮጵያ

«ኩዊር ኢትዮጵያ» የተለያዩ ፆታዊና ወሲባዊ ዝንባሌ ላላቸው ኢትዮጵያዊ ኩዊር ሴቶች እንዲሆን ታስቦ በኩዊር ሴቶች የተመሠረተ አማራጭ ምኅዳር ነው። ይኸውም ሌዝቢያን፣ ባይሴክሽዋል ወይም ኤሴክሽዋል የሆኑ ሴቶችንንና ትራንስ ሴቶችን ያካትታል። ይህ ምኅዳር የኩዊር ማኅበረሰብ ታሪክ እና የሕይወት ልምድ ትልቅ ሥፍራ የሚይዝበት ነው። እንደ' ኩዊር ማኅበረሰብ የዕለት ተዕለት ሕይወታችንን ገጠመኞች፤ የተለያዩ ሰዎችን የግል ታሪኮች፤ ቃለ- መጠይቆች እንዲሁም ሥነ-ጥበባትን እንደምናካትት ተስፋ እናደርጋለን። ከነዚህ በተጨማሪም በኢትዮጵያ ውስጥ እና በዳያስፖራ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ቤተሰቦች ራሳቸውን ሆነው የሚመጡበት የበይነ-መረብ ማኅበረሰብ መድረክ ሆኖ እንዲያገለግል ማስቻል ፍላጎታችን ብቻ ሣይሆን ጥረታችንም ጭምር ነው።

queerethiopia.com

ethioqueer

QueerEthiopia

etqueerfamily@gmail.com

# የአርታዒያን መልዕክት

“ራሳችንን መቀየር ሳያስፈልገን ከምንወዳቸው ሰዎች ጋር በምንፈልገው መንገድ በአልን ማክበር ነፃነት ነበር” ስትል አንዷ ባለታሪካችን ከተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞቿ ወይም የመረጠቻቸው ቤተሰቦቿ ጋር በአልን እንዴት እንደምታከብር በማስታወስ ትናገራለች። ሌላዋ “የመረጠቻቸው ቤተሰቦቿን” እንደ “እውነተኛ ቤተሰቦቿ” ትገልጻቸዋለች።

‘’የተመረጡ ቤተሰቦች”  ህጋዊ እውቅና ቢያገኙም ባያገኙም እርስ በርስ ለመደጋገፍ እና ፍቅር ለመስጣጠት በፍቃደኝነት የሚፈጠር የስጋ ዝምድና የሌለው ትስስር ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ ሀገራት በሚገኙ ማህበረሰቦች ውስጥ የተመረጡ ቤተሰቦች አስፈላጊነት ከቃላት በላይ ነው።

ወደ ንስንስ አምስተኛ እትም እንኳን በደህና መጡ። ይህ እትም የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ጓደኝነት በህይወታችን ላይ ስላለው የተለያዩ አስተዋጽኦዎች ለመወያየት የተዘጋጀ ነው። ከመረጥናቸው ቤተሰቦቻችን ጋር ተሞክሮዎችን ስለምንጋራባቸው የተለያዩ መንገዶች እና እንዴት ህይወታችንን ይበልጥ አስደሳች እንዲሆን እንደሚያስችሉን እንወያያለን። በዚህ የንስንስ እትም ላይ በምንሰራ ወቅት እንደተረዳነው የተወለድንበትን ቤተሰብ ብንወድም ማንነታችን እንድንሆን ነፃነትን የሚሰጠን የመረጥናቸው ቤተሰቦቻችን ናቸው።

“ልዩነቱ ግልጽ ነው፣ ነፃነት። ነፃነት ይሰማሻል’ ስትል እድላዊት የመረጠችው ቤተሰቧ ከትውልድ ቤተሰቧ ጋር ስታወዳድር የተሰማትን ትገልጻለች። ሌላው በዚህ እትም የዳሰስነው ርእስ ብዙ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ከቀድሞ የፍቅር አጋሮቻቸው ጋር በጓደኝነት ለመቀጠል ስለመምረጣቸው ነው።  በጸሎት የቀድሞ ፍቅረኞች በህይወታችን ውስጥ ስለሚጫወቱት አስፈላጊ ሚና ምን አይነት ድጋፍ፣ ጓደኝነት እና የምናድግበትን ቦታ እንደሚሰጡን በመግለጽ ታስረዳለች።

ሌላ ባለታሪካችን ጓደኛነት የጋራ እሴቶች ስለመጋራት መሆኑን ታስታውሰናለች። የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነት እና ኢትዮጵያዊነት የሚያመሳስለን ነገር ቢሆንም ጥልቅ የሆነ ወዳጅነት ለመመስረት ግን ብዙ የምንጋራቸው አመለካከቶች ሊኖሩን ይገባል። “የተለያየ እሴት ካለው ሰው ጋር ጓደኝነት መመሥረት አይቻልም። እሴቶች እርስ በርሳችን እንዴት እንደምንግባባ፣ እንደምንተያይ እና አንዳችን ለሌላው የምንሰጠውን ቦታ ይወስናሉ” ስትል ጽፋለች።

ሌሎች ርእሶቻችን ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪን ስናገኝ ወደነበረን ጊዜ እና ተሞክሮውን ተከትሎ ስለሚመጡት ስሜቶች ያስታውሱናል። ለመጀመሪያ ጊዜ ስለነበረን ቆይታ እና ‘የኔ’ የምንለውን ቦታ ስናገኝ የነበረውን ስሜት እንድንናፍቅ ያደርገናል።

በዚህ የንስንስ እትም “የተመረጡ ቤተሰቦች” እንዴት እንደአዲስ መረዳት እንደምንችል እና ማን መካተት እንዳለበት እንማራለን። ከባለታሪኮቻችን አንዷ የስጋ ቤተሰቧ “የተመረጠው ቤተሰቧ” ውስጥ እንደሚካተት ትናገራለች። “የኛን ማህበረሰብ እኔ እንዲሰማኝ የሚያደርጉትን የእኔነት ስሜት ትልቅ ቦታ እሰጥዋለሁ። የስጋ ዘመዶቼ የሚሰጡኝ የደህንነት ስሜት ሁለቱ በአንድ ላይ መሄድ እንደሚችሉ እንዲሰማኝ አድርጓል።” ሌላዋ ባለታሪክ የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ጓደኛዋ ከመረጠቻቸው ቤተሰቦቿ አንዷ እንደሆነች ታስረዳለች።

እንደተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነታችን አብዛኞቻችን ቤታችንን በሌሎች የማህበረሰቡ አባላት ውስጥ ወይም  በመረጥናቸው ቤተሰባችን ውስጥ ለመገንባት ትስስርን እንፈጥራለን። ለአብዛኞቻችን የመረጥነው ቤተሰባችን ወሳኝ ነው ምክንያቱም የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪነትን ብቻ በትክክለኝነት በሚፈርጅ ዓለም ውስጥ ሁሌም የሚያጋጥመን መገለል ቢኖርም ህይወታችንን በአግባቡ ለመኖር እንድንችል የሚረዳን መከላከያችን ነው።

በነዚህ የንስንስ ገፆች ውስጥ ራሳችሁን እንደምታገኙ እና ስለ ቤተሰብ እና ጓደኝነት በአዳዲስ እና ሰፊ መንገዶች ለማሰብ እንደምትበረታቱ ተስፋ እናደርጋለን።

እንደተለመደው በዚህ የንስንስ እትም ላይ የተሳተፋችሁትን ሁሉ እናመሰግናለን። ታሪኮችን ከመጻፍ እስከ ቃለ መጠይቅ በማድረግ፣ ፎቶግራፍ ማንሳት፣ ከስእል ጥበብ፣ ከአርትዖት እስከ መተርጎም፣ እንዲሁም በማንበብ ለተሳተፋችሁ ሁሉ ምስጋናችን ከልብ ነው። ንስንስ እውን የሆነችው በእናንተ ነው።

መልካም ንባብ!

# ቤተሰቦቻችንን
# መምረጥ





“

**ከተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞቹ ጋር ይህን ያህል ቅርበት የለኝም፣ መናገር የሌለብኝ ነገሮች ይኖራሉ ...**

ዮዲት

“ጥፋት ቢኖርባትም ባይኖርባትም ማሂ ከኔ ምንም የምትደብቀኝ ነገር የለም። ከእህቶቼ በላይ ለሷ ቅርብ ነኝ። እና በጣም የምትረዳኝ ሰው አድርጌ ነው የማስባት እሷም እንደዛው” ስትል ዮዲት ከጓደኛዋ ማሂ ጋር ስላላት ግንኙነት ትናገራለች።

ዮዲት የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ኢትዮጵያዊት ስትሆን በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ስላለው በምርጫ የሚገኙ ቤተሰቦችን የተመለከተ ጽንሰሀሳብ በቀላሉ ማሳየት ችላላች።

ማሂና ኮኪ ካሉበት የሶስት ጓደኛማቾች ግሩፕ ውስጥ አንዷ ነች። በብዙ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደተለመደው ዮዲት ከማሂ ጋር የተገናኘችው ከስድስት አመት በፊት በፌስቡክ ሲሆን በኢንተርኔት የነበራቸው ጓደኝነት አድጎ ስለደህንነታቸው መተማመን ሲችሉ በአካል ለመገናኘት በቁ። የስድስት አመት ወዳጅነታቸው የጀመረው ማሂ ለዮዲት ደፍራ የጓደኝነት ጥያቄ በፌስቡክ ስትልክ ነበር።

“እኔና ማሂ ጓደኞች እንሆናለን ብለን አስበን አናውቅም እንደውም እኔ በደንብ አላናግራትም ነበር በፌስቡክ የጓደኝነት ጥያቄ ስትልክልኝ ራሱ የመለስኩላት ቆይቼ ነው። ከዛ ግን ስልክ ተቀያይረን ማውራት ጀመርን፣



ከዛም በደንብ ተግባባን” ስትል ዮዲት ታስታውሳለች።

ዮዲት እና ኮኪ ከሶስት አመታት በፊት ሁለቱም በሚያውቋቸው ጓደኞች በኩል ነው የተዋወቁት። ብዙ የሚያመሳስላቸው ነገር በመኖሩ እና በኢንተርኔት ብዙ ጊዜ ስለሚያወሩ ጓደኝነታቸው ጠነከረ።

ሶስቱ ጓደኛሞች በነጻነት እርስበርስ ያወራሉ፣ በቀላሉ ይስቃሉ። እርስበርስ ከመቀላለዳቸው በተጨማሪ ያሳፍራሉ ስለሚሏቸው ትውስታዎች አናወራም ሲሉ በጨዋታ መልክ ይናገራሉ። ይሁንና ሁሉም ለጓደኝነታቸው ስላላቸው ግምት እና በተለይም እንደተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነታቸው ይህ ጓደኝነት ስለሚሰጣቸው ድጋፍ እና መረዳት ለማውራት ደስተኛ ናቸው።

‘ከተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞቼ ጋር ይህን ያህል ቅርበት የለኝም፣ መናገር የሌለብኝ ነገሮች ይኖራሉ፣ ከማሂ ጋር ያለኝ ጓደኝነት ግን ለየት ይላል፣ በህይወቴ ያለውን ነገር ሁሉ የምነግራት ለሷ ነው።’ ስትል ዮዲት ትናገራለች።

‘የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞች ማፍራቴ ይበልጥ እውነተኛ ለሆነ ወዳጅነት በር ከፍቶልኛል’ ትላለች ኮኪ። የጓደኞቿ ባህሪ እና ህይወትን የሚመለከቱበት መንገድ ጓደኝነታቸውን በመገንባት እና በማስቀጠል ላይ ተጽእኖ ቢኖረውም ኮኪ የሚያስፈልጋትን ድጋፍ እና ራሷን የምትሆንበትን ቦታ ማግኘት ችላለች።

የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ጓደኝነት ያለውን ቦታ ሌላ በአዲስ አበባ የምትኖረው የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዋ ቤቲ እንዲህ ትገልጸዋለች። በምርጫችን ቤተሰብን ማግኘት ትልቅ ነገር እንደሆነ እና ራስን ለመሆን የሚመች አካባቢን እንደሚፈጥር ትናገራለች።

ብዙ የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞች ቢኖሯትም ለተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞቿ ለየት ያለ ቦታ ትሰጣለች። ከተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ



“

**አሷን ካገኘሁዋት በኋላ ሚስት ስጠኝ ብዬ መጸለይ ራሱ አንደምችል ተረዳሁ።**

**ቤቲ**

ጓደኞቿ ጋር ግልጽ ሆና ስሜቶቿን መግለጽ አለመቻሏ አንዱ ምክንያቷ ነው። እውነትን መናገር ሊያስከትል የሚችለውን ችግር ስለምታውቅ ከፍቅረኛዋ ጋር ከተለያየች በኋላ ስታስዝን እንኳን ለምን እንዳዘነች ግልጽ ሆና መናገር ይከብዳታል።

"ከተቃራኒ ጾታ አፍቃሪዎች ጋር ደስ የሚል ጊዜ ማሳለፍ ይቻላል፣ እንደማንኛውም ሰው ትስቂያለሽ ትዝናኛለሽ ትበያለሽ ትጠጪያለሽ ግን ከልብሽ የምታወሪው ወሬ አይኖርሽም ለምሳሌ እኔ ስለማፈቅራት ሴት ማውራት አልችልም። ከኛ ማህበረሰብ ጋር ግን ማውራት እችላለሁ" ስትል ቤቲ ትናገራለች።

ለቤቲ በምርጫዋ ያገኘችው ቤተሰቧ፣ እንዲሁም የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ራሷን ከእምነቷ እና ከጾታዊ ዝንባሌዋ ጋር ማስታረቅ እንድትችል ትልቅ አስተዋጽኦ እንዳለው ታስረዳለች። የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ መሆኗን ካመነች በኋላ  ይህ ጥሩ ክርስቲያን ከመሆን ጋር የማይጣጣም እንደሆነ ስለተሰማት ሀይማኖቷን መከተል ከብዷት ነበር። ወደ ቤተክርስቲያን መሄድም አቁማ ነበር።

"በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ማህበረሰብ ውስጥ በመሆኔ እግዚያብሄር አይሰማኝም ወይም እግዚያብሄር ማጥፋት ከሚፈልጋቸው ነገሮች አንዷ እኔ ነኝ ብዬ አስብ ነበር" ትላለች ቤቲ።

ከራሷ ጋር ያደረገችው ምክክር እምነቷን እንድትቀበል ባለማድረጉ እግዚአብሔር የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎችን አይወድም ስትል ደምድማ ነበር። በመጨረሻ ከቤተክርስቲያን እና ከሃይማኖቷ ጋር ያላትን ግንኙነት ሙሉ በሙሉ እንዳታቋርጥ እና ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖራት ያደረጋት ከጓደኛዋ ጋር የነበራት ወዳጅነት ነው። ቤተክርስትያን አቅራቢያ የመሄድ ፍራቻዋን ማጥፋት እንደቻለች ትናገራለች።

"እሷን ካገኙሁዋት በኋላ ሚስት ስጠኝ ብዬ መጸለይ ራሱ እንደምችል ተረዳሁ፣ እና ከፈጣሪ እንዳልርቅ አድርጋኛለች። የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሆኜም ቤተክርስትያን ሄጄ ማመስገን፣ መፀለይ፣ መሳተፍ እንደምችል፣ ፈጣሪ ያለበት አካባቢ ሁሉ መገኘት እንደምችል እንድረዳ አድርጋኛለች" ስትል ቤቲ ጓደኛዋን ታመሰግናለች።

> “
>
> **ስለ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነቴ ማውራት ባልፈልግ እንኳን በኛ ማህበረሰብ ውስጥ መሆን የሚቀል ስሜት እንዲሰማሽ እና እርስበርስ እንድትግባቢ ያደርጋል። ስለማንኛውም ነገር ለማውራት ነጻነት ይኖርሻል።'**
>
> **እድላዊት**

ቤቲ በምርጫዋ ላገኘቻቸው ቤተሰቦቿ ትልቅ ቦታ ትሰጣለች፣ በቻለችው መጠንም ያላትን ትርፍ ጊዜ አብራቸው ለማሳለፍ ትሞክራለች።። በስነጥበብ ውስጥ ስለምትሰራ አብዛኞቹን ቀኖቿን የምታሳልፈው በማህበረሰቡ አባላት በሚዘወተሩ ቦታዎች ነው። ቀን ላይ ጊዜ እስከምታሳልፍባቸው እና ስራ እስከምትሰራባቸው ካፌ ጀምሮ በማታ ልትዝናናባቸው የምትሄዳቸው መጠጥ ቤቶች ሁሉም በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን የሚዘወተሩ ናቸው።

እድላዊት ሌላ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ስትሆን ከሁለት አመታት በፊት በምርጫዋ ቤተሰብ ያረገችውን ሰው ማግኘት ችላለች። መጀመሪያ የተዋወቀቻት በፌስቡክ ቢሆንም በኋላ ግን በጓደኛዋ የድሮ ፍቅረኛ አማካኝነት በአካል ሊገናኙ ቻሉ። ከዛን ጊዜ ጀምሮም በጣም ተቀራርበዋል።

ለእድላዊት ከጓደኛዋ ጋር መሆን በነጻነት ሁሉንም የህይወት ገጽታዋን የምትገልጽበት ነጻነት ይሰጣታል። ከተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞቿ ጋር እንደምትሆነው ሊረዷት የሚከብዳቸውን የህይወቷን ክፍል ለመደበቅ አትገደድም።

'ልዩነቱ ግልጽ ነው፣ ነጻነት። ስለ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነቴ ማውራት ባልፈልግ እንኳን በኛ ማህበረሰብ ውስጥ መሆን የሚቀል ስሜት እንዲሰማሽ እና እርስበርስ እንድትግባቢ ያደርጋል። ስለማንኛውም ነገር ለማውራት ነጻነት ይኖርሻል።' ስትል ትናገራለች።

ነፃነት ስለማይሰማት እና ራሷን መሆን ስለማትችል አሁን ላይ ከተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞቿ ጋር ያላት ግንኙነት የተገደበ ነው። በፊት በነበራት ጓደኝነት ከነሱ ጋር ስትሆን ብዙውን ጊዜ ማሳየት

የምትችለው “ግማሽ ህይወቷን” ብቻ እንደሆነ ይሰማት ነበር። ራሷን ለመሆን ነጻነት ከማይሰጧት ሰዎች ጋር ጓደኛ መሆን በርግጥም ከባድ ነው። ይህ ከተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ጋር ጓደኛ ለመሆን እንድትመርጥ አድርጓታል። “ከሚመሳሰልሽ ሰው ጋር ጓደኝነት መመሥረት ደስ ይላል’ ስትል ምክንያቷን ትገልጻለች።

እድላዊት የቅርብ ጓደኛዋን በአካል ብታገኝም አብዛኞቹ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ግን በኢንተርኔት ብቻ ይገናኛሉ። ቤቲ ጓደኛዋን ፌስቡክ ላይ ብታገኛትም አሁን ላይ የማህበረሰቡ አባላት በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ የመገናኘት እድላቸው እንደሰፋ ትናገራለች። እድላዊት በማህበራዊ ሚዲያ ብዙ ሰዎችን አግኝታለች አሁንም በማህበረሰቡ ውስጥ ባሉ ሌሎች ሰዎች በኩል ብዙ ሰዎችን መተዋወቋን ቀጥላለች።

ስለማህበረሰቡ አስፈላጊነት አጠንክራ ብትናገርም አንዳንዶች እርስ በርስ ያላቸው ግንኙነት ላይ ጥያቄ አላት። “በእኛ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሰዎች - ሁሉንም አያካትትም - ግን ጓደኝነትን አያውቁም። ተገናኝተሽ ከተዝናናሽ ጥሩ ጊዜ ካሳለፍሽ በኋላ ቀጣዩ ነገር የፍቅር ወይም የወሲብ ግንኙነት ነው። ይህ ነገር ያስጠላኛል። መጥፎ ነው የምለው ይሄንን ነው። እንደነዚህ አይነት ሰዎች ጓደኝነትን አያውቁም ሁሉም ነገር ከወሲብ ጋር ያገናኙታል።” ስትል ትናገራለች።

ዮዲት የጓደኝነትን መሰረታዊ ነገሮች አስፈላጊነት ታስረዳለች። የወሲባዊ ዝንባሌ እና የፆታ ማንነት ምንም አይነት ቢሆን የጓደኝነት ወሳኝ ነገሮች ሁሌም የጋራ እሴቶች እና ባህሪያት እንደሆኑ ትናገራለች። ከጓደኞቿ ጋር መግባባቷ እና በጓደኝነታቸው ውስጥ መሆን ስላለባቸው መሰረታዊ መንገዶች መስማማታቸው ጓደኝነታቸው እንዲበረታ ረድቷቸዋል። ጓደኞቿም በተመሳሳይ አቅጣጫ እንደሚጓዙ ትናገራለች። በሌላ አገላለጽ ኢትዮጵያዊነት እና የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነት ብቻ የጓደኝነታቸው መሰረት






"

**አሁን የተሻለ ቦታ ላይ ነው ያለነው ብዬ አስባለሁ ... ይሁንና ከተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ወንዶች ብዙ የምንማረው ነገር ስላለ ሁላችንም የምንችለውን ማድረግ አለብን።**

**በጸሎት**

ሊሆን እንደማይችል ሁሉም ይስማማሉ።

"ዋናው ነገር ባህሪ ለባህሪ መግባባት ነው። ጓደኝነታችን ሊዘልቅ የቻለው በባህሪ ስለተጣጣምን ነው።' ስትል ዮዲት ትናገራለች።

ጓደኝነታቸው መሰረታዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ባይመሰረት ኖሮ ጓደኞች እና አንዱ ለሌላው በምርጫ ቤተሰብ መሆን አይችሉም እንደነበር ኮኪ ትናገራለች። ተጠያቂነት በመሀላቸው መኖሩ ሁሉም እንዲያድጉ የሚረዳ ጓደኝነትን ለመገንባት እና ዘላቂነት እንዲኖረው በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ ትልቅ ሚና ይጫወታል።

"ከባዱ ነገር እርስ በእርስ መረዳት አለመቻል ነው። ስለጥሩ እና መጥፎ ጎኖቻችን በግልጽ መነጋገር መቻል በጣም አስፈላጊ ነው። እርስበርስ ለመረዳዳት ደግሞ መረዳት ያስፈልጋል።' ስትል ኮኪ ትናገራለች።

አዲስ አበባ የምትኖረው የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዋ በጸሎት አብዛኛውን ጊዜዋን ከአዲስ አበባ ውጪ ያሳለፈች ቢሆንም የመረጠችው ቤተሰቧ እውነተኛ ቤተሰቧ እንደሆነ ትናገራለች። የስጋ ዘመዶቿን ብትወዳቸውም በምርጫዋ ያገኘቻቸው ቤተሰቦቿ ደግሞ ራሷን እንድትሆን የሚያስችሏት ናቸው። በዋናነት ያለችበት የተመሳሳይ ጾታ ማህበረሰብ ቦታ ወንዶች የሚበዙበት እንደሆነ እና እውነተኛ ማንነቷን የመሆን ነፃነት ሊሰጧት እንደቻሉ ትናገራለች። "ከስጋ ወንድሞቼ ጋር ስሆን እንደሚሰማኝ ከነሱ ጋር ስሆንም ኩራት ይሰማኛል"' ስትል ትናገራለች።

በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ማህበረሰብ ውስጥ ከሚገኙ ሴቶች ጋር ብዙ ጊዜ አሳልፋ አታውቅም ለዚህም ምክንያቷ ምቾት ስለማይሰማት እንደሆነ ትናገራለች። አንዷት የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ጓደኛዋ የማህበረሰቡ ሴቶች በጋራ የሚገናኙበት ዝግጅት እንዳለ ብትነግራትም ለመታደም ስታመነታ ቆይታለች።

"ብዙ የድሮ ፍቅረኞች አንድ ላይ የሚሰባሰቡ መስሎ ይሰማኛል። በርግጥ የኔ ባይሆኑም ግን የማውቃቸው ሰዎች የድሮ ፍቅረኞች ናቸው። ይህ ትንሽ ምቾት ይነሳኛል። ከወንዶች ጋር ስሆን ግን የሆነ ነጻነት የሚሰማሽ ነገር አለ። ባላቸው ነገር ኩሩ ስለሆኑ አንቺም በሰውነትሽ አታፍሪም። ብዙ ከሴቶች ጋር ስሆን እርስበርስ ስለምንወዳደር የጎደለኝን ነገር የማይ ይመስለኛል።' ስትል በጸሎት ትናገራለች።

ስለራስ ሰውነት ያለ ግንዛቤ እና ሴቶች እርስበርስ ይገማመታሉ የሚለው ጠቅላይ አመለካከት የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሴቶች በሚገናኙባቸው ቦታዎች እንዳትገኝ አድርጓታል። ይሁንና እነዚህ ሴቶች የሚገናኙበት እና ማህበረሰባቸውን የሚገነቡበት አስተማማኝ ቦታዎችን መፍጠር አስፈላጊ መሆኑን አፅንዖት ሰጥታ ትናገራለች።

"አሁን የተሻለ ቦታ ላይ ነው ያለነው ብዬ አስባለሁ። በርግጥ አሁንም ብዙ የሚቀረን ነገር አለ ግን ጥሩ ጅማሬ ነው። እንደበፊቱ እየተወዛገብን አይደለም ራሳችንን አምነን ተቀብለን ኑሮዋችንን እየመራን ነው። ይሁንና ከተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ወንዶች ብዙ የምንማረው ነገር ስላለ ሁላችንም የምንችለው ማድረግ አለብን።'' ስትል በጸሎት ትናገራለች።

በቅርቡ በአዲስ አበባ የተካሄደው የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሴቶችን ያካተተ መጠነኛ ስብሰባ መተሳሰር እና በምርጫ ቤተሰብ መሆን ድጋፍ እና ፍቅር የተሞላበት ማህበረሰብ መፍጠር እንደሚያስፈልግ የሚያመላክት ነበር። ለጥቂት ተሰብሳቢዎች ይህ ዝግጅት ከሌሎች ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሴቶች ጋር ለመገናኘት የመጀመሪያ አጋጣሚያቸው ነበር።

"በግልጽነት የምታዋሪው እና ተሞክሮሽን የምታጋሪው ሰው ማግኘት መቻል፤ ደስ የሚል ነው። እንደዚህ አይነት ጓደኞች ደስ ይላሉ ይህን ደግሞ ልታገኚ የምትችይው በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ካሉ ሰዎች ጋር ብቻ ነው።" ስትል በአዲስ አበባ የምትኖረው የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዋ ሳራ ትናገራለች።



# መጀመሪያ ኩዊር ኢትዮጵያዊ ስትተዋወቁ እንዴት ነበር?

## ጋብርኤላ

መጀመሪያ በአካል የተዋወኩት ኩዊር ሰው ሰሎሜ ናት። መጀመሪያ ማንነቴን ማመን የጀመርኩበት ጊዜ ላይ ነው ሰሎሜን ያዋራኋት። እና የመጀመሪያም ሰው ናት ይሄን ነገር ሞራል ኖሮኝ ለመናገር የደፈርኩት። እኔ ስለቀለለችኝ ነው የነገርኳት ግን ከዛ በኋላ ነው ሰው ለማግኘት ፍላጎቱን ያገኘሁት።

ሳገኛት ደስ ብሎኝ ነበር፣ አሁን እኛ ማህበረሰብ ላይ ለአንዳችን የሚሰማንን ነገር ብቻ ሳይሆን ሁላችንም ላይ ያለ ስሜት ነው የሚመስላኝ። እኔን የሚመስሉኝ ሰዎችን ሳገኝ ነው ደስ የሚለኝ ብዙ ጊዜ።

## ፂዮን

ለመጀመሪያ ጊዜ ያገኘኋት ሴት ሊዲያ ትባላለች፤ የድሬ ልጅ ነበረች። የተዋወቅነው በፌስቡክ ነበር። መጀመሪያ ስለማንኛውም ነገር ዝም ብለን እናወራ ነበር። ከሆነ ጊዜ በኋላ ግን ሌዝቢያን ነኝ ብላ ነገረችኝ። በቃ ነገሮች በሙሉ ተቀይረው ፎንቃ በፎንቃ ሆንን፤ ግን የፍቅር ጓደኛ ነበራትና ሁሌ ላግኝሽ ስላት እምቢ ትለኝ ነበር።

አንድ ቀን ከጀለሶቼጋ ፒያሳ ፈታ እያልን ዝም ብዬ ደወልኩላት። የት እንዳለሁ ስነግራት እሷም እዛው አካባቢ እንዳለች ነገረችኝ። ከዛም ለመጀመሪያ እና ለመጨረሻ ጊዜ ተገናኘን። አሪፍ ምሽት አሳለፍን። በማግስቱ ደውላ ያለችበት እንድመጣ ነገረችኝ። እኔ ግን ስላልተመቸኝ ልሄድ አልቻልኩም። ምን እንደተፈጠረ ባይገባኝም ከዛ በኋላ መጠፋፋት ጀመርንና ጭራሽ ማውራት አቆምን።

# ማህበረሰቦችን መገንባት

## - የቀድሞ ፍቅረኞች እንደ ጓደኞች -



የህና አዲስ ፍቅረኛዋ ሴት ጋር መግባባት ከብዷት ነበር። ብዙ አለመግባባቶች በመሃላቸው በመኖሩ ብዙ ጊዜ ትበሳጭ ነበር። ችግሮቹን ለመፍታት የሚረዳት ሰው ማናገር ነበረባት። እናም የድሮ ፍቅረኛዋን አናገረቻት።

የቀድሞ ፍቅረኛዋ አብራ ያለቻትን ሴት በደንብ እንድታዳምጥ እና ነገሮችን በእሷ አይን ለመረዳት እንድትሞክር መከረቻት። የህናም ፍቅረኛዋን በደንብ ለመስማት እና ሁኔታዎችን ከእርሷ አንፃር ለመመልከት ተነሳሳች። ይህም በመጨረሻ ሁለቱ እንዲስማሙ አድርጓቸዋል። የህና ከቀድሞ ፍቅረኛዋ ጋር ባደረገችው ንግግር በመነሳሳት ከፍቅረኛዋ ጋር ታርቃ አብረው መቀጠል ችለዋል።

በኢትዮጵያ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ማህበረሰብ ውስጥ ከቀድሞ ፍቅረኛዎች ጋር በጓደኝነትን መኖር የተለመደ ነው። እ.አ.አ. በ 2017 በአር ኤል ግሪፊዝ እና ባልደረቦቹ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከተቃራኒ ጾታ አፍቃሪዎች ይልቅ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ከቀድሞ የፍቅር አጋሮቻቸው ጋር ጓደኛ ሆነው ይቆያሉ።

ኢትዮጵያዊት የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ የሆነችው በጸሎት ለዚህ ማሳያ ናት።

“እኔ ብዙ የድሮ ፍቅረኞች አሉኝ፤ በጣም ብዙ! እና ከአብዛኛዎቹ ጋር ጥሩ ጓደኞች ነን። ለሻይ/ቡና ተገናኝተን ስለግል ችግሮቻችን በነፃነት እናወራለን ልንፈታቸውም እንሞክራለን። ከአብዛኞቹ ጋር ጠንካራ ወዳጅነት አለኝ’ ስትል ትናገራለች።

የህና ከአብዛኞቹ የቀድሞ ፍቅረኞቿ ጋር ከሞላ ጎደል ጓደኛ ሆና ቆይታለች። የግንኙነቱ መጨረሻ በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ጠብ ካልተቀየረ በስተቀር፣ ከቀድሞ ፍቅረኞቿ ጋር ጓደኝነት መቀጠሉ እንደሚጠቅም ታስባለች።

“ከድሮ ፍቅረኞቼ ጋር በሰላም መለያየትን እመርጣለሁ። አብዛኞቹ

“

**ከቀድሞ ፍቅረኞችሽ ጋር ጓደኝነትን አለመፍጠር ትርጉም የለውም። ማህበረሰቡ ትንሽ ስለሆነ ከነሱ ከራቅሽ ብቻሽን ነው የምትሆኚው፣ ማንን ታማክሪያለሽ?**

**በጸሎት**

አሁንም ጓደኞቼ ናቸው ማለት እችላለሁ። በጣም ቅርብ ባንሆንም ቢያንስ ሰላም እንባባለን” ብላለች የህና።

በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ማህበረሰብ ውስጥ ያሉ ሴቶች ከቀድሞ ፍቅረኞቻቸው ጋር ጓደኛ ሆነው የሚቆዩበት አንዱ ምክንያት ባሉት ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነው። ማህበረሰቡ በጣም ትንሽ ስለሆነ ከቀድሞ ፍቅረኛቸው መራቅ እንደአጠቃላይ ከማህበረሰቡ መራቅን ሊያስከትል ይችላል። የህና በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ማህበረሰብ ውስጥ ብዙ ሰዎች የሚተዋወቁ በሌሎች በኩል እንደሆነ ታስረዳለች። የቀድሞ ፍቅረኞቿ በማህበረሰቡ ውስጥ ካሉ ሌሎች ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሴቶች ጋር አስተዋውቀዋታል።

“የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪዎች የድሮ ፍቅረኞቻቸውን ማየት ባይፈልጉ ሌሎች ምርጫዎች ያላቸው ይመስለኛል። በኛ ማህበረሰብ ግን ራሳቸው የተቀበሉ ሴቶች ጥቂት በመሆናቸው ከነሱ ለመራቅ ከወሰንሽ ብቻሽን ትቀሪያለሽ” ስትል የህና ታስረዳለች።

ይህ ከቀድሞ የፍቅር አጋሮች ቢያንስ የተለመደ ሰላምታ እንዲኖር የሚያስገድድ መሆኑ ሳለ የህና እና በጸሎት ጓደኝነትን መመስረቱም ጥቅም እንዳለው ይረዳሉ። የህና ከቀድሞ ፍቅረኞቿ ጋር የገነባችው ወዳጅነት ተጨማሪ ድጋፍ እንዳላት እንዲሰማት አስችሏታል። የቀድሞዋ ፍቅረኞቿ “የተመረጡ ቤተሰቧ” አባላት ናቸው። ምክር ትጠይቃቸዋለች፣ አብራ የምትዝናናቸው እና በእውነተኛ ማንነቷ በነጻነት አብራቸው ልትሆን የምትችላቸው የቅርብ ሰዎቿ ናቸው።

በጸሎት እዚህ ላይ “ከቀድሞ ፍቅረኞችሽ ጋር ጓደኝነትን አለመፍጠር ትርጉም የለውም። ማህበረሰቡ ትንሽ ስለሆነ ከነሱ ከራቅሽ ብቻሽን ነው የምትሆኚው፣ ማንን ታማክሪያለሽ? ይልቁንም ያለውን ጥላቻ ትቶ ጓደኛ መሆን ነው የሚሻል። ምክንያቱም

“

**... አየቆየ ሲሄድና መቁረጥ ግዴታ ሲሆንብሽ አብረሽ የነበረሽን ነገር እየረሳሽ ትሄጃለሽ። ከዛም አብሮሽ የሚቆየው የነበረሽ መግባባት ብቻ ይሆናል።**

ዮሀና

የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞችሽ ጋር ስትሆኚ ሁሌም ማንነትሽን መደበቅ ያስፈልግሻል። ከተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሰዎች ጋር ስታወሪ ግን ያንን ድብቅ ማንነትሽን ማየት ይችላሉ። ይህ ደግሞ በጣም አስፈላጊ ስለሆን መራራቅ የለብንም ብዬ አስባለሁ” ስትል ትናገራለች።

ይህ ማለት ግን በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ሁሉ ከሁሉም የቀድሞ ፍቅረኞቻቸው ጋር ጓደኛ ሆነው ይቀጥላሉ ማለት አይደለም። ለበጸሎት የረዥም ጊዜ እና የተዋሳሰበ የፍቅር ግንኙነት ከነበራት የቀድሞ ፍቅረኞቿ ጋር በጓደኝነት መቆየት ቀላል አይደለም። ግንኙነታቸው የፍቅረኝነት ገጽታውን ሳይለቅ እና ችግሮቻቸውን ሳይፈቱ መቆየት ስሜታችንን ሊጎዳ ይችላል የሚለው አንዱ ፍርሀቷ ነው።

ከቀድሞ ፍቅረኝነት ወደ ጓደኝነት የሚደረገው ሽግግርም ሁሌም ቀላል አይደለም፤ ይዞት የሚመጣው ደስ የማይል ስሜት ሊኖር ይችላል።

“መጀመሪያ ላይ ከባድ ነው። አብረሽ እያለሽ የነበረሽ ስሜት ወዲያው እንደተለያየሽ አይለቅሽም። ከመጀናጀኑም ነገር አትወጪም... ከሌላ ሴት ጋር ስታያት ደግሞ ያምሻል.. የመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራቶች ይከብዳሉ። ግን እየቆየ ሲሄድና መቁረጥ ግዴታ ሲሆንብሽ አብረሽ የነበረሽን ነገር እየረሳሽ ትሄጃለሽ። ከዛም አብሮሽ የሚቆየው የነበረሽ መግባባት ብቻ ይሆናል” በማለት ዮሀና ታስረዳለች።

ማንነቷን ከመቀበሏ በፊት ወንዶች የፍቅረኞች ነበሯት ዮሀና ከእነሱ ጋር ጓደኛ ሆና እንዳልቀጠለች ትናገራለች። ጓደኛ ላለመሆን የመረጠችበት ዋና ምክንያት ከነሱ ጋር የነበራት ግንኙነት ጥልቀት ያለው ባለመሆኑ ነው።

“ከወንዶች ጋር አፈቅርሃለሁ አፈቅርሻለሁ ከመባባል ባለፈ ምንም ስለሌለው ከተለያየሽ በኋላ የሚያስተሳስርሽ ነገር አይኖርም። ከሴቶች ጋር ግን የበለጠ መግባባት እና ግንኙነት መፍጠር ትችያለሽ።”

ይህም የቀድሞ ፍቅረኞች ከመሆን ባለፈ ትርጉም ያለው ወዳጅነት በመተማመን በመፍጠር እና እርስ በርስ ድጋፍና ምቾት እንዲሰጣጡ አስችሏቸዋል።





# መጀመሪያ ኩዊር ኢትዮጵያዊ ስትተዋወቁ እንዴት ነበር?

## ራሄል

መጀመሪያ የተዋወኳትን ኩዊር ሴት ስሟን አላስታውስም። ከአራት ዓመት በፊት በፌስቡክ ላይ ነበር የተዋወቅነው። ስንተዋወቅ ዝም ብለን እናወራ ነበር፤ መጀናጀን ግን አልነበረም። በአካል ስንገናኝ ለአንድ ሰዓት ተኩል አካባቢ አብሬያት ቁጭ ብዬ ነበር። ሙሉ ሰውነቴን ነበር የነዘረኝ። ይቅርታ ግን በጣም ነበር የተፀየፍኳት። እኔንጃ በቃ... አልወደድኳትም።

ማንነቷን አልወደድኩትም። ስናወራ የነበረችው ልጅ እና ያገኘኋት ልጅ ሌላ ሰዎች ነበሩ ። በመልክ ምናምን ሳይሆን በባህሪዋ። በቃ ሁለት የተለያዩ ሰዎች ማለት ናቸው። ደሞ በዛ ሰዓት እንዴት አወቅሽ እንዳትይኝ ግን ጥሩ ሰው እንዳልሆነች ስሜቴ በደንብ ነግሮኛል። ከሄድኩም በኋላ በብዙ ተግባሮች እንደዛ አይነት ሰው መሆኗን አረጋግጫለሁ።

በመገናኘታችን ምንም ደስተኛ አልነበርኩም። ለረጅም ጊዜም ከዛ በኋላ [ኩዊር] ሰው ማግኘት አልፈለኩም ነበር። እስከዛሬም ድረስ ምንም አይነት ልምድና [ኩዊር] ጓደኛ እንዳይኖረኝ የሆነበት ምክንያት እሷ ናት። እሷ የፈለገችው ነገር ስለነበረ የሆነው እራሴን እንድፀየፍ ነበር የረገችን። አይ... ምንም አልወዳትም!

## ኤልሳ

ለመጀመሪያ ጊዜ ኩዊር የሆነ ሰው ያገኘሁት መቲን ነበር። ደስታና ነፃነት ተሰምቶኝ ነበር። “እኔ ብቻዬን አይደለሁም” የሚለውን ሃሳብ እንዳሰብኩም ትዝ ይለኛል!

## ኤደን

መጀመሪያ የተዋወኳት ሴት ናርዶስ ትባል ነበር። ብዙም ኮሚኒቲው ዉስጥ አልነበረችም፤ ማንም አያውቃትም ነበር። የተገናኘነው ከአስራ አራት ዓመት ገደማ በፊት ነበር። እንዳጋጣሚ ተዋወቅንና ተግባባን። እኔ ስለዚህ ሕይወት ምንም ነገር አላውቅም ነበር። እሷ ነች የነገረችኝ። ከዛ በኋላ ግን ወደድኩት እና ቀጠልኩበት።

ከጊዜ በሁኋላ ግን ደብረኝና ለማቆም የቻልኩትን ያህል ሞክሬ ነበር። ወደ ሰባት አመት አቁሜም ነበር። ከዛ ግን ደግሜ ተመለስኩ። ያው ግን አሪፍ ትውስታ ነው ያለኝ።

# የጓደኝነት ፖለቲካ





ጓደኝነት ለተለያዩ ሰዎች የተለያየ ትርጉም ሊኖረው ይችላል። የምንተማመንበት፣ የምናማክረው፣ ጥሩ እና መጥፎ ጊዜያትን አብረን የምናሳልፈው ሰው ሊሆን ይችላል። ወደተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ስንመጣ ግን ጓደኝነት ከዛም የበለጠ ትርጉም አለው። የስጋ ዘመዶቻችን በማንነታችን በሚያገሉን ሰአት የምንፈልጋቸውን ሰዎችን መርጠን ቤተሰብ የምናደርግበት መንገድ ነው።

በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የተመሳሳይ አፍቃሪዎች የሚጠሉበት ሀገራት ለምንኖር ሰዎች ጓደኝነታችን ከማንነታችን ጋር የሚያስተሳስረን የህይወት ገመድ ነው። ለብዙዎቻችን፣ በእውነት መቶ በመቶ እራሳችንን የምንሆንበት ብቸኛው ጊዜ ከጓደኞቻችን ጋር ነው።

የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ መሆናችን አንድ የምናጋራው ነገር ቢሆንም ስለየተለያዩ ነገሮች የተለያየ አመለካከት እና አቋም ይኖረናል። እነዚህ ልዩነቶቻችን በሀገራችንና በአለም ላይ አዳዲስ ክስተቶች ሲፈጠሩ ጎልተው ይታያሉ። ያኔ ታዲያ ጥያቄው ተመሳሳይ የፖለቲካ አመለካከትን ከማይጋራን ሰው ጋር ጓደኛ መሆን እንችላለን? ይህ ሁላችንም ከራሳችን እና ከጓደኞቻችን ጋር ልናደርገው የሚገባ በጣም ከባድ ውይይት ነው፣ በተለይም የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ እና ኢትዮጵያዊ ስንሆን።በእድገታችንና በመሠረት ዓመቶቻችን ብዙ ጓደኞች አፍርተናል የጾታ ዝንባሌያችንን/የወሲብ

> “
>
> **ጓደኝነትን ስገልጸው አንድ ሰው ያለገደብ ወይም ፍርሃት በእውነት ራሱን ሊሆን የሚችልበት የደግነት ቦታ ነው።**

ዝንባሌ ሙሉ በሙሉ ከመረዳታችን በፊት እና በእድገታችን ወቅት ብዙ የፖለቲካ አመለካከታችን ላይጋሩ ወይም የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ የሚጠሉ እና በማንነታችን ምክንያት ሊቀበሉን ከማይፈልጉ ብዙ ሰዎች ጋር ጓደኝነት መስርተን ሊሆን ይችላል።

ከኔ ጋር በፖለቲካ አመለካከት ከሚለያዩ ሰዎች ጋር ጓደኛ ስለመሆን ጥያቄ ሲቀርብልኝ ሁልጊዜ የምጠይቀው “የየትኛው ፖለቲካ ነው?” ብዬ ነው። እያወራን ያለነው የገበያና የኢኮኖሚ ፖሊሲው ወይም በአገሪቱ የመንግሥት መዋቅር ላይ የተለየ አመለካከት ያለው ሰው ከሆነ መልሴ “አዎ! ከእንደዚህ ዓይነት ሰው ጋር ጓደኛ መሆን እችላለሁ” ነው። በመቀጠል ስለየአመለካከቶቻችንን ጥቅሞች እና ጉዳቶች መወያየት እንችላለን። ነገር ግን ሰዎች በፆታ ማንነት፣ በወሲብ ዝንባሌ፣ በዘር እና በጎሳ ላይ

ተመስርቶ በሕግ እኩል መብትና ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል በሚለው ላይ የተያየ 'አመለካከት' ያለው ሰው ከሆነ ጓደኛ መሆን አንችልም። በዚህ ጉዳይ ላይ ላለመስማማት መስማማት አይሰራም። ይህ የአመለካከት ልዩነት አይደለም፣ በአጭሩ ሲቀመጥ የእሴት እና የሞራል ልዩነት ነው።

ጓደኝነትን ስገልጸው አንድ ሰው ያለገደብ ወይም ፍርሃት በእውነት ራሱን ሊሆን የሚችልበት የደግነት ቦታ ነው። ይህም እርስበርስ መከባበር እና መዋደድ ወደሚለው ይወስደናል። ከስጋ ዝምድና በተለየ ጓደኝነት ራሳችን የምንገነባው፣ የምንመርጠው እና ልናቆየው ከፈልግን ልንንከባከበው የሚገባ ነው። አንድ ጓደኛ ከሌላኛው ማንነቱውን ከደበቀ ጓደኝነትን መገንባት የማይቻል ይሆናል። ጓደኛሞች አንድ ሰው ነፃ እንዲሆኑ የሚያስችል ቦታ መስጠት አለባቸው እንጂ በእንቁላል ቅርፊት ላይ እንደመራመድ የሚያሳቅቅ እና መገለልን እንዲፈሩ የሚያደርግ መሆን የለበትም። እንዲሁም አስተያየቱ እና ንግግሮቹ የስነልቦና ጉዳትን ሊያስከትሉ ከሚችሉ ሰው ጋር ያለመሆንን ነፃነት ሊሰጥዎ ይገባል። በእኔ እምነት የተለያየ እሴት ካለው ሰው ጋር ጓደኝነት መመሥረት አይቻልም። እሴቶች እርስ በእርሳችን እንዴት እንደምንቀራብ፣ እንዴት እንደምንተያይ እና አንዳችን ለሌላው የምንሰጠውን ቦታ ይወስናሉ። አንድ ሰው ሰብአዊ መብቶች እንደሚገባው ሙሉ ሰው ከማያየው ሰው ጋር ጓደኛ ሊሆን ይችላል ብዬ አላምንም።

ታዲያ ይህን ትልቅ የፖለቲካ ለውጥ ከጓደኝነት ጋር በተያያዘ እንዴት እንመለከተዋለን? የፌስቡክ ጓደኝነትን መግታት ቀላል ሊሆን ይችላል፣ ግን ለመገንባት ዓመታት የፈጁን ማህበራዊ ትስስሮች ማቆም እጅግ ከባድ ነው። መረጃዎች እንደሚያሳዩት ደግሞ ከእኛ ጋር ከማይስማሙ ጋር ያለንን ግንኙነት ማቋረጥ ካሰብነው ተቃራኒ የሆነ ውጤት ሊኖረው ይችላል ምክንያቱም ማህበረሰባዊ ለውጥ እንዲፈጠር ልናሳምናቸው የሚገባው እነሱን ነው። ይሁንና በባህል እና በሃይማኖት ውስጥ በተዘፈቁ ብዙ የተሳሳቱ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን የተመለከቱ ሀሳቦቻቸውን እንዲቀይሩ ሰዎችን መታገል አስቀድሞ ለተሸነፈ ጦርነት እንደ መታገል የሚቆጠር ነው። ማንም ሰው በጓደኝነት ውስጥ የራሱን ቦታ ለማግኘት መታገል የለበትም። ወዳጅነት ከዕለት ተዕለት ጦርነቶቻችን ዕረፍት ለመፈለግ የምንመጣበት፣ ድጋፍን የምናገኝበት እንጂ ልንታገልለት የሚገባ አይደለም።

> “
>
> **እኛ እንደ ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነታችን በጓደኛነታችን ውስጥ የፖለቲካ ተጽእኖን ተረድተን አንዳንድ ነገሮችን ’ላለመስማማት መስማማት’ በሚል የምናልፋቸው እንደማይሆኑ ማወቅ ነው።**

ስለዚህ አሁን ራሳችንን ከእነዚህ የቀድሞ ጓደኞቻችን እንዴት መጠበቅ እንደምንችል ማወቅ አለብን። ይህ ለመልመድ ከባድ ሊሆን ይችላል። ከዚህ ቀደም በጣም ግልጽ ከነበሩለት ሰው ራስን መከላከል ነው ግን የአእምሮ ጤናን ለመጠበቅ ሲባል መሆን ያለበት ነው። የቀድሞ ጓደኝነቶቻችንን ቀስ በቀስ መቀነስ እና መተዋወቅ እና መተማመንን የምንገነባበት ነጥብ ላይ እስከንደርስ ድረስ ግልጽ የሆኑ የማይታለፉ መስመሮች እንዲኖሩ በማድረግ በእሴቶቻችን ላይ ስምምነት ላይ መድረስ ወይም ወደ ቀድሞው ጓደኝነት መመለስ በማይቻልበት ደረጃ ድረስ መወሰን መቻል አለብን።

በጊዜው ግን ያጣነውን ለመተካት አዳዲስ ጓደኝነቶችን መመሥረትና የነበሩንን መንከባከብ አለብን። እነዚህ ጓደኝነቶች ጤናማና ራሳችንን ለመሆን ደኅንነት የሚያስማን እንዲሆኑ ማድረግ አለብን። ጓደኝነታችን ተመሳሳይ እሴት እና ቅርርብ ላይ የተመሰረተ እና ፖለቲካዊ አመለካከታቸው ህይወታችን ወይም ነጻነታችንን አደጋ ውስጥ የማይጥል መሆን አለበት።

እኛ እንደ ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነታችን በጓደኛነታችን ውስጥ የፖለቲካ ተጽእኖን ተረድተን አንዳንድ ነገሮችን “ላለመስማማት መስማማት” በሚል የምናልፋቸው እንደማይሆኑ ማወቅ ነው። ጓደኝነቶች መገንባት ያለባቸው በጠንካራ የመተማመን፣ የጋራ እሴቶች እና በእውነተኛ ማንነታችን ላይ የተመሰረተ ፍቅር ላይ ነው።

# በማህበራዊ ገጾች ላይ ...



# ... ቤትን ማግኘት

> “
>
> **በአማርኛ ፊደላት መልክት መጻጻፍ፣ መቀለድን እና የሌላ ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሰውን አስተሳሰብ በአማርኛ ማንበብ የመሳሰሉ ትንንሽ ነገሮች ለኔ ምን ያህል ቦታ እንዳላቸው ተረዳሁ።**

የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ስለመሆኔ ራሴን የመቀበል ጉዞዬን እንዳፋጥን እና በዙሪያዬ የሚቀበሉኝ ሰዎች እንዲኖሩኝ የኢንተርኔት መገናኛ መንገዶች ረድተውኛል። ቋሚ የማህበራዊ ትስስር ገጾች ተጠቃሚ አይደለሁም ግን በቂ ግንዛቤ አለኝ። ለረጅም ጊዜ የምስራቅ አፍሪካዊ ወይም የጥቁሮች የሆኑ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ገጾችን ስከታተል ቆይቻለሁ፣ አናግሬያቸው ግን አላውቅም። አደረኩ ቢባል ፖስቶቻቸውን ላይክ ወይም ሼር ማድረግ ነው። በኢትዮጵያ የሚገኙ ቤተሰቦቼን ለመጎብኘት በወሰንኩ ጊዜ ግን ምናልባት ቤተሰቦቼ በጣም ሀይለኛ ቢሆኑብኝ ሌሎች የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ወይም ከጎኔ ሊሆኑ የሚችሉ ሰዎች ለደህንነቴ እንደሚያስፈልጉኝ ተረዳሁ። እንዴት አድርጌ ሰዎችን ላገኝ እችላለሁ ብዬ በምጨነቅበት ጊዜ አንድ ጓደኛዬ ኢንስታግራም ላይ ከምከተላቸው ገጾች አንዱን እንዳናግር ነገረኝ። እዛው ኢንስታግራም ላይ መልእክት መጻፍ ስለከበደኝ የሚያውቁት ነገር እንዳለ የሚጠይቅ ኢሜይል ላኩላቸው።

በዛ ኢሜይል ህይወቴ ተቀየረ። በመልሳቸው ፍርሀቴን ተቀብለው ስሜቴን እንተረዱኝ ገለፁልኝ። በዛች ኢንተርኔት ግንኙነት ብቻ ከመቼውም በላይ የታየሁ መስሎ ተሰማኝ። ከዛም አዲስ አበባ ከምትኖር የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ጋር አገናኙኝ። ከዚህች ሴት ጋር ለተወሰነ ጊዜ ኢሜል ከተደራረግን በኋላ ወሬያችንን ወደ ፌስቡክ ሜሴንጀር ወሰድነው። ወዲያው በደንብ ተግባብተን በአንድ ባህል ውስጥ እንዳደጉ ሁለት ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ገጠመኞቻችንን  ረዘም አድርገን መወያየት ጀመርን። የራሴን ነጸብራቅ እንዲህ በጥራት ማየት እችላለሁ ብዬ አስቤ አላውቅም ነበር። ምክንያቱም በኢንተርኔት ከማውቃቸው ሰዎች ጋር አውርቼ አላውቅም፤ ኢትዮጵያውያን የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ምን አይነት ህይወት እንዳላቸው የማውቀው በተወሰነ መልኩ ብቻ ነበር። ኢትዮጵያ ውስጥ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሆኖ ከሚኖር ሰው ጋር በቀጥታ ማውራት መቻሌ ህይወቴን ቀይሮታል። በአማርኛ ፊደላት መልክት መጻጻፍ፣ መቀለድን እና የሌላ ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሰውን አስተሳሰብ በአማርኛ ማንበብ የመሳሰሉ ትንንሽ ነገሮች ለኔ ምን ያህል ቦታ እንዳላቸው ተረዳሁ። ከዚህ ቀደም ለእኔ ያልደረስኩበትን በዉበትም ሆነ በሃዘን የተሞላውን የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነቴን ስሜት የከፈትኩ መስሎ ተሰማኝ።

ከዛች ልጅ ጋር አሁንም እናወራለን፣ ደስ የሚል ጓደኝነት አለን። ለተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ጥላቻ ባለበት ሀገር ውስጥ ማንነቷን በፈለገችበት መንገድ ለመኖር ያላት ቆራጥነት እኔም የፍቅር አጋር እንድፈልግ አበረታታኝ። የኢንተርኔት የፍቅር አጋር መፈለጊያ ገጽ ስከፍት እና የተለያዩ ሰዎችን ሳገኝ ሁሌም ከጎኔ ነበረች። ከመገናኘታችን ጥቂት ወራት በፊት ግን የፍቅር አጋር መኖር የማይታሰብ መስሎ ይሰማኝ ነበር። ከጓደኛዬ ጋር የማደርጋቸው ንግግሮች ህይወቴን ሙሉ ለሙሉ ቀይረውታል። በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነቴ የተረጋጋሁ እና የምተማመን እንድሆን ሆኛለሁ። ራሴን በፈለኩት መንገድ ለመግለጽ አይከብደኝም። ሄጄ ያገኘኋቸው ሰዎች ጋር የነበረኝ ቀን ወደ ፍቅር እና ወሲባዊ ግንኙነቶች አላደጉም ግን ጓደኞች ሆነናል።

ያ ጥርጣሬ የተሞላው አንድ የምስራቅ አፍሪካ የማህበራዊ ሚዲያ ገጽን መከተል ወደኢሜል ማድረግ፣ ይህ ደግሞ ወደፌስቡክ መልክት ልውውጥ፣ ከዛም ዘላቂ ነው ብዬ ተስፋ ወደማደርገው ጓደኝነት መርቶኛል። ይህ ጓደኝነት ህይወቴ ብሩህ እንዲሆን እና በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነቴ በነጻነት እንድኖር ብርታቱን ሰጥቶኛል። ዛሬ አስቤ ከማውቀው በላይ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞች አሉኝ። ደፋር እና ቁርጠኛ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች የማህበራዊ ሚዲያ ገጾችን ባይመሰርቱ ኖሮ በዙሪያዬ እነዚህ ህይወትን የሚቀይሩ ጓደኞች አይኖሩኝም ነበር።

# በአጋሮቻችን ውስጥ ማህበረሰቦችን ማፍራት



> **አኔም ደሞ ከ ‘ሌላኛው’ ህይወቴ በስተቀር ስለ ካምፓስ ህይወት ሁሉንም ነገር አነግራት ነበር። ቢሆንም፣ ከሴት ፍቅር እንደያዘኝ ልነግራት አልቻልኩም።**

ከስምንት ዓመታት በላይ በጓደኝነት ቆይተናል። መጀመሪያ የተዋወቅነው በማህበራዊ ሚዲያ ስለነበር፣ የፌስቡክ ፅሁፎች, ቪዲዮዎችን እና የሙዚቃ ክሊፖችን እንላላክ ነበር። ሁለታችንም የምንጋራው የሙዚቃ ፍቅር ስለነበረን ለመግባባት በጣም ቀላል ነበር።

የዘሪቱ ከበደ አልበም እየተሸጠ የነበረበት እና ብዙ የሚደመጥበት ጊዜ ነበር። ዘፈኖቿን አብረን እየዘፈንን እናደንቃት ነበር። እኔ ከአዲስ አበባ ውጭ የዩኒቨርስቲ ተማሪ ስለነበርኩ እና እሷ ደግሞ እዚህ ትሰራ ስለነበር ጓደኝነታችን የርቀት ነበር እናም ለረዥም ጊዜ አልተገናኘንም። በአካል ከመገናኘታችንም በፊት ግን በሚገርም ሁኔታ ተቀራርበናል። ስለ ቤተሰቦቻችን፣ ቀኖቻችን፣ አብረን ስለሆናቸው ወንዶች፣ ስለ ስራዋ እና እኔ በካምፓስ ስለማሳልፈው የምሽት ህይወት እያወራ ነበር። አዲስ አበባ ስለሚከፈቱ አዳዲስ ካፌዎች እና ሬስቶራንቶች መረጃዎች ሁሉ ትሰጠኝ ነበር። ይሁንና ስለኔ የጾታዊ ግንኙነት ምርጫ አውርተንበት አናውቅም።

ወጣት፣ ግራ የተጋባሁ፣ እና ስለራሴ እርግጠኛ ያልሆንኩ ነበርኩ። ራሴን የማወቅ ጉዞዬ በብዙ እፍረት፣ ራስን በመጥላት እና በብቸኝነት ስሜት የተሞላ ነበር። ለሌሎች ማካፈል የማልችለው ነገር የሆነ እና የተቃራኒ ጾታ አፍቃሪ ለመሆን ራሴን “የመፈወስ” ጉዞ ሆኖ ነበር የሚሰማኝ። ከብዙ ወንዶች ጋር መሆን ይረዳኛል ብዬ አስብ ስለነበር፣ ሆንኩ። ብቻዬን ብጸልይ ነፃ የምወጣ እየመሰለኝ ብዙ ጸለይኩ። አብሬያት ለነበርኩት ሴት በጭራሽ አንስቼባት አላውቅም። እሷም የማንነት ጥያቄ ይኑርባት አይኑርባት አላወኩም። በጣም የብቸኝነት ጊዜ ነበር። ለማንኛውም ራሴን ለመቀበል የነበረውን አሳዛኝ ወቅት ልተወው ምክንያቱም አሁን መናገር የምፈልገው ታሪኬ እሱን አይደለም።

ለዮዲት፣ ለፌስቡክ ጓደኛዬ ይህን ለመናገር  ነጻነት አልተሰማኝም። ራሴን ሙሉ ለሙሉ ባልተረዳሁበት ሁኔታ እንዴት አድርጌ እንደምናገረው አላወኩም።

ለመጀመሪያ ጊዜ የተገናኘንበትን ቀን አስታውሳለሁ። ከትምህርት እረፍት ወደ አዲስ አበባ ከተመለስኩ በኋላ አንድ ቀን ከሰአት ቡና ልንጠጣ ወሰነን። ሆዳችንን እስኪያመን ስንስቅ ቆየን፣ ለዓመታት የምንተዋወቅ ያህል መስሎ ስለተሰማኝ ሁሌም ጓደኞሞች እንደምንሆን ታውቆኝ ነበር። እርስ በርሳችን ተቀላለድን፣ ቅልል ያለ ስሜት ነበረው። ትልቅም ይሁን ትንሽ ስለሚያስፈሩን እና ስለሚያሳፍሩን ነገሮች አወራን፣ በጣም ተቀራረብን። አዲስ አበባ በሄድኩ ቁጥር አብረን እናሳልፋለን፣ ወደዩኒቨርስቲ ስመለስ ደግሞ በቫይበር እና ፌስቡክ እናወራለን።

ስለቀኖቻችን እና ስለግል ህይወታችን ሁሌም እናወራለን። ሁሉንም ግንኙነቶቿን፣ መጥፎ የፍቅር ግኙነቶቿ እና በአሪፍ ሁኔታ ስላረገችው ወሲብ ሁሉ አውቅ ነበር። ህይወቷ ውስጥ ያሉትን ወንዶች ስም አውቃለሁ። ስለሚከተሉት ፋሽን እንኳን አልቀረኝም። እኔም ደሞ ከ”ሌላኛው” ህይወቴ በስተቀር ስለ ካምፓስ ህይወት ሁሉንም ነገር እነግራት ነበር። ቢሆንም፣ ከሴት ፍቅር እንደያዘኝ፣ ከሴት ጋር እንደተኛሁ እና ከሴት ጋር ወሲብ መፈጸም ምን አይነት ስሜት እንዳለው ልነግራት አልቻልኩም። ሀፍረቴ ይህን እንዳላደርግ ከለከለኝ። ይህ ገጽታዬ በእኔና በአምላኬ መካከል ተደብቆ ነበር።

ጓደኝነታችንና ስለ ተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነቴ ያለኝ ግንዛቤ እያደገ ሄደ። ስለ ራሴ የበለጠ ማወቄን ስቀጥል፣ ቀስ በቀስ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነቴን ከእምነቴ ጋር ማስማማት ቻልኩ። እኔ በራሴ አለም ውስጥ ነበርኩ። በአራት አመታት ጓደኝነታችን ከእፍረት እና የጥፋተኝነት ስሜት ብነሳም ወደ ኩራት እና ነፃነት ስሜት መድረስ ችያለው። እሷ ግን ምንም አላወቀችም። እኔ ከሐሙስ እስከ እሁድ የምጨፍር እብድ ሴት ስሆን፣ ስለሱም ለዮዲት የማካፍላቸው ብዙ ታሪኮች ነበሩኝ። በዛ የብቸኝነት መንገድ



ራሴን እንዴት እንዳቆየሁ አላውቅም። ተመርቄ ወደ አዲስ አበባ ከተዛወርኩ በኋላ ይህን የራሴን ገጽታ ለመደበቅ ከብዶኝ ነበር። ዮዲት አብሬ ከምሆናቸው ወንዶች ጋር መሆን ምን ያህል ደስታ እንደሚነሳኝ ያስገርማት ነበር። ወንዶች ለምን እንደማልወዳቸው አልገባትም። ዮዲት ባታውቅም አዲስ አበባ ውስጥ ከሴቶች ጋር መሆን ጀመርኩ። ከአንዲት ሴት ጋር በምገናኝበት ወቅት ሌላ ቦታ እንደሆንኩ አስመስላለሁ። አምስት አመት ጓደኞች ከሆንን በኋላ ይህንን ከእርሷ መደበቅ እንደማልችል ወሰንኩ። ማንም ሰው ከጓደኝነት የሚፈልጋቸውን ነገሮች ያሟላች ሰው ነበረች ግን ስለ እኔ ካወቀች፣ እንደዛው ትቀጥላለች? ጥያቄ ሆኖብኝ ነበር።

እንዴት እንደመረጥኩት ባላውቅም አንድ ቀን ሁሉንም ነገር ልነግራት ወሰንኩ። ለመጀመሪያ ጊዜ ስለተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪነቴ ነገርኳት። ማንነቴን እንደምትደብቅልኝ ተስፋ አድርጌ ነበር። ጓደኝነታችን ይህን መቋቋም እንደሚችል እና ይበልጥ እንደሚያድግም በልቤ ተስፋ አደረኩ። ስለራሴ ነግሬያት ከጨረስኩ በኋላ ዮዲት ምንም አይነት ጥያቄ አልጠየቀችኝም። ከሴቶች ጋር ስለመሆኔ ባለማወቋ እየቀለደች ሁኔታውን ቀለል አደረገችልኝ። “የተለመደ” ታሪክ የተናገርኩ ያህል ቀኑ እንደሁልጊዜው ቀጠለ።

አልፈልግሽም ብትለኝ ወይም ቤተሰቦቼ “እንዲታደጉኝ” ለመንገር ብትወስን ኖሮ ምን አደርግ እንደነበር እርግጠኛ አይደለሁም። እሷ ግን ማንነቴን ለመውደድ እና ለመቀበል ወሰነች። በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ ብዙ ጥላቻ ቢኖርም ዮዲት በህይወቴ ውስጥ መኖሯ ሁሉንም የተሻለ ያደርገዋል። ይበልጥ እውነተኛ እና ጠንካራ እንድሆን ትገፋፋኛለች። በጣም ድብቅ የሆነውን የራሴን ማንነት ከእሷ ጋር ካካፈልኩ በኋላ ለብዙ የቅርብ ጓደኞቼ እና እህት ወንድሞቼም እውነቱን እንድነግር አበረታታችኝ። አሁን ቤተሰቤ ናት - እህቴ። መደበቂያዬም ሆነች።

ዮዲት ብዙ ጥያቄዎች ካሏት እረፍት ከሌላት ልጅ ወደ ኩሩ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነት ሳድግ ተመልክታለች። በሁሉም ከጎኔ ነበረች። በጣም አመሰግናታለሁ። አብረን ወደ ሌላ ሃገር በምንጓዝ ጊዜም ሁለታችንም የፍቅር ጓደኞቻችንን ወደሁለት መኝታ ክፍል ያላት ሆቴላችን አምጥተናቸው አብረን ካደርን በኋላ በማግስቱም ቡና እየጠጣን እናወራበታለን፤ እንስቅበታለን። አስቡት ያለምንም ገደብ ራስን መሆን መቻል!

ዮዲት እወድሻለሁ፣ እራስሽን ስለሆንሽ አመሰግንሻለሁ፣ ለፍቅርሽ አመስጋኝ ነኝ!



# ለኛ ብቻ የሆነ በታ፣

## በአልን ከመረጥነው ቤተሰብ ጋር አብሮ ከማክበር የሚገኘው ደስታ

በአላትን ሁሌም እጠላ ነበር፡፡ ከልጅነቴ ጀምሮ፣ ከደስታና ፈንጠዝያ ይልቅ ምቾት እንደሚነሳ ነገር አየዋለሁ። እናቴ ከእያንዳንዱ በዓል በፊት እና በበአሉ ቀን መደረግ ስላለባቸው ነገሮች በጣም ትጠነቀቃለች፣ እንደዛም ሆኖ የኛ ቤተሰብ እንዳሰበችው እንዲሄድላት በማድረጉ አይሳካለትም። ሁልጊዜም በጣም ብዙ ጽዳት፣ ምግብ ማብሰል፣ መጨቃጨቅ

ከዛም በጣም ደክሞን የበአል ልብሳችንን ለብሶ ቤት በመቀመጥ ወይም በንጭንጭ በአሉን ምንም ሳንደሰት ማሳለፍ የበአሉ ገጽታዎች ነበሩ። ለምን ይህ ሁሉ ጣጣ እንደሚያስፈልግ አይገባኝም ነበር። የተሰማኝን ለመናገር ስለማልፈራ ይህንኑ እነግራቸዋለሁ፡፡

ይህ ሁሉ የተቀየረው በአልን ለመጀመሪያ ጊዜ ከተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞቼ ጋር ባከበርኩ ወቅት ነበር፡፡ በአሉ ከመድረሱ ከጥቂት ወራት በፊት፣ የቅርብ ጓደኞችን እናት ከዚህ አለም በሞት ተለየች። ያለችው ብቸኛ ቤተሰቡ እሷ ብቻ ስለነበረች ያለሷ በአልን እንዴት እንደሚያሳልፍ በጣም አሳስቦት ነበር። እናም የተወሰንን ጓደኞቹ ቤቱ ሄደን አብረነው ልናከብር ወሰንን። ሁላችንም የኮሌጅ ተማሪዎች ስለነበርን ብዙ ገንዘብ አልነበረንም ስለዚህ ሁላችንም ከየቤታችን አንዳንድ ነገር ወስደን ለማክበር ተስማማንም። የበአሉ እለት እስከ ከሰአት ድረስ ከቤተሰቤ ጋር ቤት አሳለፍኩ። በበአል እንደማያስወጡኝ ስለማውቅ የበአል የበጎ አድራጎት ስራ አለብኝ ብዬ ከሌሎቹ ጋር የምጋራውን ምግብ ይዤ በሰበብ ወጣሁ።

እኔ ከትፎ ከነቤተሰቡ፣ ሌላ ጓደኛዬ ደግሞ ዶሮ ወጥ፣ አንዱ ጥብስ ይዘን ሄድን፡፡ ወይንም ገዝተን ነበር ግን ምግቡ መሰራት ከመጀመሩ በፊት ነበር ያጋመስነው፡፡ ከበአላት ከምጠብቀው የተለየ ድባብ ነበረው፡፡ በአንድ መንገድ ብቻ እንድናከብር ያስገደደን ሁኔታ አልነበረም፣ የሚቆጣ ሰው አልነበረም፣ በቦታው የነበርነው እዛ መገኘት ስለፈለግን ብቻ ነበር እንደውም በጣም ደስ የሚል ጊዜ ነበር፡፡ አንዱ በጊዜው ለማጅ ሼፍ ጓደኛዬ አብረው የሚሄዱ የማይመስሉ ብዙ ቅመማቅመሞችን አንድ ላይ ጨማምሮ በጣም የሚጣፍጥ ጥብስ ሰራ። ምግቡ እየተሰራ እኛ አብረን እየጠጣን፣ እየደነስን ነበር፡፡ በጊዜው የነበረው ደስታ፣ ሳቅ እና በጋራ የምንመገበው የሚጣፍጥ ምግብ ከምንወደው ሰው ጋር በአልን ማክበር ምን እንደሚመስል እንድረዳ አደረገኝ፡፡ ጓደኞችን በአል ላይ ብቻውን እንዳይሆን አብረን ለማክበር እንደቀላል ያደረግነው ነገር ከመረጥኳቸው ቤተሰቦች ጋር በአላትን ሁሌ የምናከብርበት ባህል እንዲኖረን አደረገን። አሁን አስር አመት አስቆጥረናል፡፡

በአል ስናከብር ያሳለፍናቸው ብዙ አስደሳች ትዝታዎች አሉኝ። ባር ውስጥ ለማክበር ከመረጥንባቸው በዓላት በአንዱ፣ ለየጓደኞቻችን ቤተሰቦች እየደወልኩ የአንዱ ጓደኛችን እናት እንደሆንኩኝ አስመስዬ ለሊቱን አንድ ላይ 'እኔ ቤት' እንዲያድሩ ሳስፈቅድ ትዝ ይለኛል። በርግጥ እውነታው አብዛኞቻችን በጣም በመስከራችን እና ጥሩ ጊዜ እያሳለፍን በመሆኑ ወደቤት መሄድ አለመፈለጋችን ነበር። በሌላ በአል ደግሞ የአንዱ ጓደኛችን ቤት እያከበርን ጎረቤቱ የጠየቃትን ድስት ለመስጠት ወደቤቱ መጥታ ስትገባ ሁሉም ወንዶች ሽርጥ አድርገው ምግብ ሲሰሩ ሴቶቹ ደግሞ ሶፋ ላይ ተቀምጠን ስናወራ አገኘችን። ፊቷ ላይ በነበረው ግራ መጋባት ምን ያህል እንደሳቅን ትዝ ይለኛል። የዛኑ እለት ምሽት የሰራውን ምግብ ይዞ ሄዶ ምን ያህል ጎበዝ ምግብ አብሳይ እንደሆነ አሳያት። የተሳሳተ የሥርዓት-ፆታ አመለካከትን የሚሰብር ትንሽ ድል!

> “
>
> **ራሳችንን እንድንሆን በማይፈቅድልን ማህበረሰብ ውስጥ ከራሳችን፣ ከአጋሮቻችን እንዲሁም አብረውን መሆን ከሚፈልጉ ሁሉ ያለፍርሀት መገናኘት የሚችሉበትን ቦታ መፍጠር ችለናል።**

አብረን ስላሳለፍነው ጊዜ በጣም ደስተኛ ነኝ። ራሳችንን እንድንሆን በማይፈቅድልን ማህበረሰብ ውስጥ ለራሳችን፣ ለአጋሮቻችን እንዲሁም አብረውን መሆን ለሚፈልጉ ሁሉ ያለፍርሀት መገኘት የሚችሉበትን ቦታ መፍጠር ችለናል። ራሳችንን መቀየር ሳያስፈልገን ከምንወዳቸው ሰዎች ጋር በፈለግነው መንገድ በአልን ማክበር ነጻነትን ይሰጣል። በነዚህ አመታት ውስጥ ህይወቶቻችን እና ጓደኝነታችን በአልን የምናከብርበትን መንገድ ቀይሮታል፣ አሁንም ግን በተለይም በበአል ወቅት ከስጋ ዘመዶቻችን ጋር እንደምናደርገው ለዚህኛውም ቤተሰባችን ጊዜ መስጠት ቅድሚያ የምንሰጠው ነገር ነው። የበአሉ አይነት፣ ሀይማኖታችን፣ ያለንበት ቦታ፣ የጓደኝነታችን ይዘት ምንም አይነት ቢሆንም ለኛ ትርጉም በሚሰጥ መልኩ በአላት የምናከብርበትን መንገድ እንፈልጋለን። አንዳችን ለአንዳችን በዚህ መልኩ ቦታ እንዳለን ማወቁ ስለበአላት ያለኝን አመለካከት እንቀይር እና በጋራ ለማክበር የተሻለ ሰው እንድሆን ረድቶኛል - እድሜ በዙሪያዬ ላሉት ሰዎች!



# ከምንነት በላይ።

# እሴቶቻችንን ማመጣጠን

> **ሞኝነት ቢመስልም የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ጓደኝነት በአለም ላይ እንዳለ እንደማንኛውም የሰው ልጅ ተሞክሮ ነው። ... ተመሳሳይ ማንነት መጋራታችሁ ብቻ በራሱ በቂ አይደለም።**

ሀበሻ ሆኖ ማደግ እና የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ መሆንን ማወቅ አግላይ የሆነ ስሜትን የሚፈጥር ነው።

ለመጀመሪያ ጊዜ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞቼን ባገኘሁ ወቅት በሁሉም መንገድ እንደታየሁ ተሰማኝ። በመጨረሻም በባህሌ ውስጥ ከሚገኙ ሰዎች ራሴን መደበቅ የለብኝም ብዬ አሰብኩ። መጠንቀቅ ያለብኝ መስሎ አልተሰማኝም፤ ግልጽ እና አዳዲስ ጓደኝነትን ለመፍጠር ጓግቼ ነበር።

የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ጓደኝነት ደስ የሚል ነው። ሀበሻ እና የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ሆናችሁ በሚመሳሰል ሁኔታ ውስጥ የሚገኙ ጓደኞችን ስታገኙ በሃበሻ ማህበረሰቡ ውስጥ ከሚገኙ ሌሎች ሰዎች ይበልጥ እንደሚረዷችሁ ይሰማችኋል። ነገር ግን ማንኛውን አይነት ጓደኝነት መከባበር ያለው እና መስመር ያላለፈ እንዲሆን ካላደረግን ሁኔታዎችን ከባድ ሊያደርግ ይችላል።

ኩዊር ጓደኝነት ስሜታዊ ደህንነት እንዲሰማችሁ እና ራሳችሁን ለመሆን ነጻነት እንዲኖራችሁ ያደርጋል። መጀመሪያ ላይ ከተዋወኳቸው ሰዎች ጋር ሁሉ ጓደኛ አብሶም የቅርብ ጓደኛ መሆን እፈልግ ነበር። ምንም ነገር አልገመግምም ነበር። የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ እና ሀበሻ መሆናቸው ለኔ በቂ መስሎ ይሰማኝ ነበር።

ጊዜው እየሄደ ሲመጣ ግን የጓደኞቼ ብዛት እየቀነሰ መጣ። ጥሎች መፈጠር ጀመሩ፣ የሚጎዱ ቃላቶች ተሰነዘሩ፣ እናም ከአንድ ከፍ አድርጌ ከማስባት የድሮ ጓደኛዬ ጋር በጣም ተጣላሁ።

የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች መሃል ያለ ጓደኝነትን ከመጠን ባለፈ አድናቆት ልንመለከት እንችላለን። አንዳንዴም ከሌሎች መከባበር እና ፍቅር ከሞላባቸው ጓደኝነቶቻችን በላይ አድርገን ልናስበው እንችላለን።

ከጓደኞቼ ጋር በመጣላቴ የፈጠረው አንድ ጥሩ ነገር በመጨረሻ አይኔን መክፈቱ ነው። የተሳሳተ መነጽሬን አውልቄ ትክክለኛውን እውነታ ስመለከት በጣም ጎድቶኝ ነበር። ለነዚህ ጓደኝነቶች ራሴን ሰጥቼ ነበር ምክንያቱም ተመሳሳይ የሆኑ እሴቶች እንዳሉን አስብ ስለነበር። ሞኝነት ቢመስልም የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ጓደኝነት በአለም ላይ እንዳለ እንደማንኛውም የሰው ልጅ ተሞክሮ ነው።

ሰዎችን በደንብ ማወቅ አለብን። አንዳንድ ጓደኞች ለናንተ የሚሆኑ አይደሉም፣ እናንተም ለነሱ አትሆኑም። ተመሳሳይ ማንነት መጋራታችሁ ብቻ በራሱ በቂ አይደለም።

ጓደኝነት አሁንም ለእኔ በጣም ልዩ ነገር ነው፤ አሁን ግን የምረዳበት መንገድ የተለየ ነው። ጓደኝነት እንዲሳካ ጠንካራ መሰረት ሊኖረው ይገባል። ለእኔ የተሻለ የሚሰራው ጓደኝነት በነዚህ ነገሮች ላይ የተመሰረተ ነው፤ መስመርን አለማለፍ፣ ተመሳሳይ እሴቶችን መጋራት፣ መከባበር እና ፍቅር ያለበት።

ግልጽ ንግግር ከሌለ፣ መስመር የሚታለፍ ከሆነ እና አንዳቸው በአንዳቸው የሚጠቀሙ ከሆነ ጓደኝነቱ መልካም ያልሆነ ይሆናል።

የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ከሆኑ እና ከናንተ ባህል ከመጡ ሰዎች ጋር አንድነትን ለመፍጠር መጓጓት ሊኖር ይችላል። ይሁንና በኋላ ላይ ግን ያልጠበቃችኋቸው ሰዎች ሆነው ከተገኙ ባላሰብነው መንገድ ሊጎዳን ይችላል። የሚያዋጣው መጀመሪያ ሰዎች እንደሰውነታቸው መገምገም እና አብራችሁ የምትሄዱ መሆናቸውን መወሰን ነው።

አሁንም ድረስ የሚወዱኝ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ጓደኞች አሉኝ። አንዳይነት እሴቶች የምጋራቸው ብዙ ጓደኞች ስላሉኝ እድለኛ ነኝ። መጨረሻቸው ያላመረው ቢያሳዝነኝም፣ እነዚህን ውብ ጓደኞቼን ይበልጥ እንዳመሰግናቸው አድርጎኛል።

# የመረጥነው ቤተሰብ

የኛ ቤተሰብ



እኔና አንድ የቤተሰብ ጓደኛዬ አንድ ካፌ ውስጥ ተቀምጠን በወቅታዊ ጉዳዮች እና በተለይም በአሜሪካ ስለተፈቀደው የተመሳሳይ ጾታ ጋብቻ ላይ ስለሚያተኩር ዜና እየተወያየን ነበር። ስለ መብት ተነስቶ ስንወያይበት የነበረው ርእስ በድንገት ወደቁጣ አዘል ክርክር ተቀየረ፤ ምክንያቱ እሱ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነት ስህተት መሆኑንና እና መቀመጫ የተፈጠረው ለወሲብ ስላልሆነ ግንኙነቱ ልክስክስነት እንደሆነ በንዴት መናገር በመጀመሩ ነበር፡፡

ምክንያት ብሎ ያተተልኝ ነገር ስላበሳጨኝ “አንተ መቀመጫህን መስጠት ካልፈለግክ አትስጥ፤ በተረፈ የሰዎች መኝታ ላይ ወጥተህ ወሲብ አደራረጋቸውን ልዳኝ ማለት አትችልም! ያንን ማድረግህ በራሱ ልክስክስነት ነው!” ብዬ የንዴት ድምፄን ሳላባብል መለስኩለት።

በተጨናነቀው ካፌ ውስጥ ያሉ ሰዎች በሚያዩን የግርምት አስተያየት አፍሮ እና ቃላት አጥሮት ነበር፡፡ እንደዛም ሆኖ ድምፁን ዝቅ አድርጎ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ መሆን ስህተት የሆነው ‘በተፈጥሮ የተሰጡን የአካል ክፍሎች አጠቃቀም’ ላይ ተመስርቶ እንደሆነ በማስረገጥ መሟገቱን ቀጠለ። እየተከራከርን በአካባቢው የነበረች እህቴ ተቀላቀለችን። ስለ እኔ የተሳሳተ “የተመሳሳይ ጾታ ደጋፊነቴ” ለማሳመን እንደምትረዳው በማሰብ በመምጣቷ ደስተኛ ነበር፡፡ በጉጉት ስለምን ስናወራ እንደነበር እና ‘ወደትክክለኛው’ መንገድ እንድትመራኝ ነገራት። እህቴ ልክ እንዳበደ ሁሉ በግርምት ተመልክታው ሌሎች ሰዎች ህይወታቸውን እንዴት እንደሚኖሩ ወይም እሱ እንደሚለው ምን አይነት ወሲብ እንደሚፈጽሙ ለመወሰን ምን መብት እንዳለው ጠየቀችው። እኔና እህቴ “ግብረ ሰዶማውያንን” ለመደገፍ መስማማታችንን ማመን አልቻለም።

የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ መሆን ምንም ችግር እንደሌለው ይበልጥ ለማሳመን ከእህቶቼ ለአንዷ ደግሞ

> “
>
> **እውነቱን ለመናገር የዛን ቀን አስፈላጊ መስሎ የታየኝ የእሱ ማመን አለማመን ሳይሆን እህቶቼ የሰጡኝ የምቾት ስሜት ነው። ቤተሰቦቼን በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነቴ ሁሌም ከጎኔ ስለሆኑ እና ይህ ሁኔታም ለኔ የሚሰጡኝን ቦታ ስላሳየኝ በጣም ደስተኛ ነኝ።**

ደወልኩ። ስናወራበት ስለነበረው ርእስ ጠቅለል አድርገን ከነገርናት በኋላ ‘እንዴ! በዚህ ዘመን እንዴት እንደዚህ ታስባለህ?’ ስትል ጠየቀችው። የሚናገረው ጠፍቶት ቤተሰቡ እንዳለ የሚያስበው ተመሳሳይ ነገር እንደሆነ ጠየቀን፡፡ ሁለቱም እህቶቼ ቤተሰባችን ሰዎች የመረጡትን ህይወት የመኖር መብት እንዳላቸው እንደሚያምን እና የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ መሆን ምንም ችግር እንደሌለው እንደሚያስብ ነገሩት፡፡

እህቴ ከሱ ጋር ንግግሯን ቀጥላ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን በተለይም በኢትዮጵያ ስለሚጋፈጡት አደጋ በመንገር አስተሳሰቡ የተሳሳተ መሆኑን ለማስረዳት ስትጥር መመልከት ጀመርኩ።

እህቶቼ ለዚህ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ተቃዋሚ ሰው ትክክለኛውን ሁኔታ እንዲረዳ ለማድረግ መጣራቸውን አደነኩ፡፡ ውይይታችን የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያንን በተለየ መልኩ እንዲያይ ያድርገው ወይም ስለጾታ እና ተመሳሳይ ጾታ ፍቅር “የተለመደ” ከሰው ሰው የሚለያይ የወሲብ፣ የፆታ ዝንባሌ እና የፆታ ማንነት  ልዩነት መሆኑ እንዲረዳ ያስቻለው እርግጠኛ አይደለሁም። .

እውነቱን ለመናገር የዛን ቀን አስፈላጊ መስሎ የታየኝ የእሱ ማመን አለማመን ሳይሆን እህቶቼ የሰጡኝ የምቾት ስሜት ነው። ቤተሰቦቼን በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነቴ ሁሌም ከጎኔ ስለሆኑ እና ይህ ሁኔታም ለኔ የሚሰጡኝን ቦታ ስላሳየኝ በጣም ደስተኛ ነኝ፡፡ በዙሪያዬ ያለው የተመሳሳይ አፍቃሪያን ጥላቻ ከመጠን በላይ እየጨመረ ሲሄድ መጠጊያዬ መሆናቸውን እንድገነዘብ አድርጎኛል።

አጋርነታቸው በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ማህበረሰብ ውስጥ ስላለው “የተመረጡ ቤተሰቦች” ጽንሰ-ሀሳብ እንዳስብ ያደርገኛል። የኛን ማህበረሰብ እኔ እንዲሰማኝ የሚያደርጉትን የእኔነት ስሜት ትልቅ ቦታ እሰጥዋለሁ። የስጋ ዘመዶቼ የሚሰጡኝ የደህንነት ስሜት ሁለቱ በአንድ ላይ መሄድ እንደሚችሉ

እንዲሰማኝ አድርጓል። እንደተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ የስጋ ቤተሰቦቻችን ደህንነት እንዲሰማን ያደርጉናል ብሎ መጠበቅ በጣም ከባድ ነው። ቤተሰቦቻችን የምንኖርበት ኢትዮጵያዊ ባህል አካል ናቸው። ይህም ማለት በተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች መገለል ላይ ንቁ ተሳታፊ ሊሆኑ ይችላሉ ማለት ነው። በአብዛኛው የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነትን ‘በጸሎት ለማስለቀቅ’ ወይም ወደዚህ የመራንን ‘ሰይጣን’ ‘ከውስጣችን ለማባረር’ በሚል ወደ ሀይማኖታዊ ቦታዎች ለመውሰድ ቀዳሚዎቹ ቤተሰቦቻችንን ናቸው። አንዳንድ ጊዜም የቤተሰብ አባላቸው ከተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነት ‘ለማስተው’ በሚል በግድ እንዲያገቡ ያደርጋሉ። የስጋ ቤተሰባችን የሚያደርጓቸውና የማያደርጓቸው ነገሮች ብዙውን ጊዜ ለብዙዎቻችን የፈተና እና የመከራዎቻችን ምንጮች ናቸው።

የእኔ የስጋ ቤተሰቤ ይህ ሁልጊዜም እውነት እንዳልሆነ ማሳያ ናቸው። ለኔ ድጋፍ ለመሆን የወሰኑ ከብዙ አንዴ ብቻ የሚገኙ ምሳሌዎች ናቸው። በስጋ መዛመዳችን እጣፈንታ ቢሆንም ከጎኔ ለመሆን ሁሌም መጣራቸው በፍላጎት መርጠው የሚያደርጉት ነገር ነው። ለእኔም ከተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ቤተሰቤ ጋር ‘ከተመረጡ ቤተሰቦቼ’ ውስት እነሱን ማካተቴ አስቤበት እና መርጬ ያደረኩት ነገር ነው።



# አስደሳች
## ነጸብራቅ





# የ20 አመት ጓደኝነት: ኩዊር ኢትዮጵያዊ ሴትን ለመጀመሪያ ጊዜ ማግኘት

ማህሌትን ለመጀመሪያ ጊዜ ያየኋት በአንድ እግሬ ግድግዳ ተደግፌና እጄን አጣምሬ ከቤተሰቦቼ ሱቅ አጥር ስር ቆሜ ነበር። ማህሌት ለመጀመሪያ ጊዜ ያወኳት ኢትዮጵያዊ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ነበረች።ከእህቴ ጓደኛ መኪና ውስጥ ወርዳ ወደኔ ስትራመድ አስታውሳለሁ። ጸጉሯ አጭር ሆኖ ቲሸርት፣ የወንድ ጂንስ ሱሪ እና የወንድ ቴኒስ ጫማ አድርጋ ነበር። ልክ እንደኔ ገና ስትታይ 'ሌዝቢያን' መሆኗን ታስታውቃለች። ሁለታችንም የተለመደ ስለሴት የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪያን ያሉ ሃሳቦችን የማስታውቂያ ፖስተር ነበር የምንመስለው። በተለመደው 'በች ሌዝቢያን ፋሽን' ቀለል አደረኩት። ጭንቅላቴን ነቅንቄ 'ሄይ ማን!' አልኳት። እሷም አላሳፈረችኝም 'ሄይ ዋትስ አፕ?' አለች።

የዛን ቀን ብዙ አላወራንም ግን ከጥቂት ሳምንታት በኋላ የእህቴ ጓደኛ በጣም ስለምትመሳሰሉ በደንብ ተዋወቁ ብላ ለምሳ ጠራችን። 'ሁለታችሁም ወጣ ያላችሁ ናችሁ፣ የ12 አመት ወንድ ልጅ ነው የምትመስሉት፣ በዛ ላይ በጣም ብዙ መጽኃፍ ታነባላችሁ።' አለችን። ከአንድ ሰው ጋር ምሳ ለመብላት እነዚህ ምክንያቶች ብቻ በቂ ባይሆኑም የእህቴ ጓደኛ የማታውቀው ግን ከማህሌት ጋር የሚያመሳስለን ሌላ ነገር እንዳለ ገምቼ ነበር።

ምሳ እየበላን ጥሩ እየተጫወትን የነበረ ቢሆንም እኔና ማህሌት ግን ብቻችንን ለመሆን ጓጉተን ነበር። እንደጨረስን የእህቴ ጓደኛ የራሷን መኪና ይዛ እንድትሄድ እና ማህሌት ደግሞ እኔን እንድታደርሰኝ ተስማማን። የምሄድበት አስር ደቂቃ ብቻ የሚያስኬድ ቦታ ቢሆንም ከአምስት ሰአት በላይ ሙሉ አዲስ አበባን እያካለልን ስንነዳ ዋልን። ከእንጦጦ ሳሪስ ከአዲሱ ገበያ ኦልድ ኤርፖርት እየተሸከረከርን ስለተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነታችን፣ እንዴት ራሳችንን እንደተቀበልን፣ ለማን እንደተናገርን፣

አዲስ አበባ ውስጥ መኖር ምንድን እንደሚመስል እና ኢትዮጵያዊነትን እና የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪነትን እንዴት እንደምንረዳው አወራን። መጨረሻ የሌለው የሚመስል ወሬ ነበር። ስለተገናኘን በጣም ደስ ብሎም ስለነበር በአምስት ሰአት ውስጥ የእድሜ ልክ ተሞክሯችንን አውርተን ለመጨረስ ያሰብን ይመስል ነበር። በዛች ሰአት ውስጥ ብቻ እንደማያልቅ ስናውቅ ስልክ ቁጥር ተቀያይረን ልናወራ ወሰንን።

ከስራ በኋላ ለቡና እየተገናኘን፣ ለሊት 8/9 ሰአት ድረስ ቆይተን ስለጥልቅ አንዳንዴም ተራ ርእሶች እንወያይ ነበር። ስለሴት ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ የተጻፉ መጽሀፎችን እንቀያየራለን። ማህሌት በፖስታ ቤት በኩል የምታስመጣቸውን ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ፊልሞች በቪዲዮ ካሴት እናያለን። በዚህ መንገድ ማስመጣቱ አደገኛ ቢሆንም ሌላ እንደዛ አይነት መጽኃፎችን እና ፊልሞችን የምናገኝበት መንገድ ስላልነበረን ደፍረን ማስመጣቱን ቀጠልንበት። በዲኤስቲቪ 'ዘ ኤል ወርድ' የተባለውን ፕሮግራም በየሳምንቱ ታይ ነበር ከዛም እድለኛ የሆኑ በሎስአንጀለስ የሚገኙ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ነጭ ሴቶች ስላላቸው ህይወት እናወራለን። ውጪ ካለው የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪ ማህበረሰብ ጋር የምንገናኘው በዚህ መልኩ ነበር፣ በድብቅ የሚገቡ መጽሃፎች፣ ፊልሞች እና ብዙም ባለመታወቁ ከአየር ላይ ባልታገደ የቲቪ ፕሮግራም በኩል።

ከጥቂት አመታት በኋላ ሁለታችንም የፍቅር አጋሮችን መያዝ ከጀመርን በኋላ ብዙ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎችን አዲስ አበባ ውስጥ ማየት ጀመርን። በአዲስ መልክ መታየት የጀመረውን የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎችን ማህበረሰባችንን ከአይናችን ፊት ሲቀየር የታየን ነበር። ማህሌት ለሴት ተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች እና የሁለቱም ጾታ አፍቃሪ ሴቶች የሚሆን የኢንተርኔት ግሩፕ ያሁ ላይ ፈጠረች፣ በዛም ብዙ የማህበረሰቡን አባላት ለማግኘት ቻልን።

> “
>
> **የምሄድበት አስር ደቂቃ ብቻ የሚያስኬድ ቦታ ቢሆንም ከአምስት ሰአት በላይ ሙሉ አዲስ አበባን እያካለልን ስንነዳ ዋልን።**

በግሩፑ ውስጥ በነበረች ሴት ምክንያት ለመጀመሪያ ጊዜ ማህበረሰቡን አንድ ላይ የሚያገናኝ የቤት ውስጥ ፕሮግራም ተዘጋጀ ይህም ትልቅ እርምጃ ነበር። ሁለታችንም ለመገኘት ፈርተን የነበረ ቢሆንም ስለመኖሩ መስማታችን ወደፊትም በቀላሉ ሊፈጠሩ ስለሚችሉ መስተጋብሮች ተስፋ እንድናደርግ አደረገን።

አሁን ላይሞቅ ያለ በአዲስ አበባ ውስጥ የሚገኝ የተመሳሳይ ጾታ አፍቃሪዎች ማህበረሰብ አባል ነኝ። በርከት ያሉ 'ወንዳወንድ' ሴቶችን አግኝቻለሁ - አንዳንዶቹ እስከ 18 አመት እድሜ የሆናሉ። በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ በነጻነት ራሳቸው ሲሆኑ እና ከሌሎች ጋር ሲገናኙ ማየቴ ደስታን ይሰጠኛል።

በርግጥ በትዝታም ይወስደኛል። የማህሌት እና የእኔ ጓደኝነት 20 ዓመታት ያህልን አስቆጥሯል። እያደግን ስንሄድ ጓደኝነታችን ተሻሽሏል እኛም የበለጠ ብልሆች ሆነናል ብለን እናስባለን። በደንብ የሚታወሰኝ ግን ለረዥም ጊዜ ብቻዋን እንደማህበረሰብ የሆነችልኝ እሷ ነበረች። የመረጥኳት ቤተሰቤ እና ብዙ ለእኔ የኩዊር ደስታ እና ነጸብራቅ ምክንያት ሆናም ቆይታለች።

“

**ለረዥም ጊዜ ብቻዋን እንደማህበረሰብ የሆነችልኝ እሷ ነበረች። የመረጥኳት ቤተሰቤ እና ብዙ ለእኔ የኩዊር ደስታ እና ነጸብራቅ ምክንያት ሆናም ቆይታለች።**

# የተመረጡ ቤተሰቦች፣ ኩዊር ጓደኝነቶች እና ማህበረሰቦች አስፈላጊ ናቸው ብለው ያስባሉ?

እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

**Um Jõñibø**

ጌታ ምስክሬ ነዉ. ሁለት ቀጥ ጓደኞች አሉኝ ዜጋ መሆኔን አምነዉ. ተቀብለዉ. አብረዉኝ ሚኖሩ የምር ከዜጋ የበለጠ እነሱ ይረዱኛል ያግዙኛል

**Dinbushea Gella**

የዜጋ ቅርብ ጓደኛ እጅግ አስፈላጊ ነው። እድሜዬ አርባን ለመንካት እየተንደረደረ ባለበት ወቅት እና ከዜጎች ጋር መተዋወቅ ስጀምር ወደ ሃያ ዓመት ሊጠጋኝ በተቃረበበት ወቅት ስለሆነ ደግሞ ይህ ጥያቄ ሊያውም እጅግ በጣም አስፈላጊ መሆኑን ያጎላዋል ብዬ አምናለሁ። ከላይ ከጠቀስኩት የእድሜ ማዕቀፍ ውስጥ መገኘቴ ብቻም ሳይሆን ሁለት አይነት ህይወት እንድኖር ስለምገደድ በዓብዛኛው ትክክለኛ ማንነቴ እና ስብዕናዬ ዜጎች ጋር ያለገደብ ስለሚገለጥም ጭምር በሃቀ የተመሰረተ ግኑኘነት ደኖረኛል። ማንነትህን ያለመከልከል የሚቀበለን ሰው መፈለግ ደግሞ ሰዋዊ ባህሪ እና አስደሳችም ነው። በህይወቴ ፈጣሪዬን የማመሰግንባቸውን ጓደኞች፣ ወንድም እህት እና ከቤተሰብም በላይ ቤተሰብ የዜግነት ህይወት ሰጥቶኛል። መወለድ ቋንቋ ነው የሚለው ብሂል እንዲገባኝ ያረገ የቅርብ ጓደኛ\ቤተሰብ አሉኝ። ሰዎች ሁሉ ይህን ቢያጣጥሙት እመኛለሁ።

**Patrick Patrick**

በጣም አስፈላጊ ነዉ ለሌላ ሰዉ መናገር የማንችላቸዉን ነገሮ ቢያንስ አብሮን ለሚመሳሰለዉ ሰዉ መናገር መተንፈስ እንችላለን እርስ በራስ እንድንደጋገፍ ያስቸለናል ሃሳብ ሼር እንድንደራርግ ያደረጋል ማለት ለእኔ በጣም አስፈላጊ ነዉ ብዬ አስባለዉ ።

**Mes Robel**

ሕይወቱን በተመሳሳይ የሚጋራ/የሚረዳ/ የቅርብ ጓደኛ ማግኘት ቢያንስ ስሜቶቻቸውን በግልፅ ማውራት ስለሚችሉ......በዋናነት ራስን ሳይሆኑ(ደብቆ) ከመኖር ከሚመጣ (ሰዎችን ራሳቸውን እስከማጥፋት የሚያደርስ) ጭንቀት በጥቂቱም ቢሆን እፎይታን የሚሰጥ ይመስለኛል

**Robin Eyoab**

as a whole "ጓደኝነት የሰው ልጅ ከሌላው መጣበቅ የመፈለግ ተፈጥሮኣዊ ግፊት መገለጫ ከራስ ሲሸሹ የሚያገኙት መጠጊያ ካለመኖር ጭቆና የአፍታ ነፃነት ማግኛ ብሶትን በቀልድ ማምለጫ ችግርን በድጋፍ መውጫ ..." ብሎ የመነበብኩት ትዝ ይለኛል ከምንም በላይ ወዳጅነት ወይም ጓደኝነት ራሳችንን የምናሳይበት እና ከሌላ ሰው ጋር የሚኖረን ጥልቅ ህብረት ነው even የፍቅር አጋር ከአፍቃሪነት ላይ ጓደኝነትንም ቢይዝ የተሻለ እንደሚሆን እናውቃለን ጓደኝነት ራሳችንን ያለኩነኔ መሆን የምንችልበት ህብረት ነው

እንግዲ ዜጋ ለሆንን ለእኛ ሁሉ ነገራችንን መሆን የማንችልበት ወይ ማሳየት የማንችልበት ሁነት ባለበት ማህበረሰብ የሚመስለን የሚረዳን እንዲሁም የሚደግፈን ወዳጅ ማግኘት እንደ እኔ የፍቅር አጋርን ከማግኘት በላይ እረፍት የሚሰጥ ነው ባይ ነኝ በእውነተኛ ጓደኝነት መሃል compromise የምናደርገው ነገር አጣዋለው ከሚል ስጋት የሚመነጭ አይደለም ለዜጋ ህይወት ጓደኝነት እኮ የሰላም መልህቅ ነው የተደበቀ ደስታችንን ማንነታችንን የምንጋራው በአንድ ብቻ ሳይሆን በሁሉ የሚደርስልን ነው ብዬ እስባለው

# የመረጥናቸው ቤተሰቦች ወይም ኩዊር ጓደኝነት አስፈላጊ ነው ብላችው ታስባላችሁ?

---

እነዚህ ምላሾች ከፌስቡክ ገፅ የተወሰዱ ናቸው ...

---

**Chav Brook**
Because sometimes they are the only one who can understand you and let you be the whole YOU .the laughter ,pain, advice and everything in between feels so comfortable and accepted 😊

ሻቭ ብሩክ

ምክኒያቱም አንዳንዴ እነሱ ብቻ ናቸው ስላንቺ ገብቷቸው ሙሉበሙሉ እራስሽን እንድትሆኚ የሚፈቅዱልሽ። ሳቁም፣ ጭንቀቱም፣ ምክሩም፣ ብቻ ሁሉም ነገር ይመቻል፤ እንዲሁም ተቀባይነት አለው።

**Lucy West**
Our Queer friendships are transformative experiences built on strength and subversion that we think, feel, experience, share, resist together lead to the emergence of queer sociality that are disproved by heteropatriarchy and yet we persist. Our coming together in solidarity and in friendship and forging solidarities through friendship is resistance. We resist by supporting each other live non normatively, counter shame privately and collectively, and share grief emphatically, helping each other navigate queerness while inhabiting and traversing inflexible structures of violence.

ሉሲ ዌስት

የእኛ የኩዊር ጓደኝነቶች በጥንካሬ እና ማፍረስ/መቀየር ላይ የተገነቡ የለውጥ ተሞክሮዎች ናቸው። በአንድነት በማሰብ፣ በመሰማት፣ በመለማመድ፣ በመጋራት፣ በመቃወም ወደኩዊር መንሰራራት የሚመራ በተባዕታይ ስርዓት ተቀባይነት ባይኖረንም እኛ ግን ፀንተናል። ከጎን በመቆምና እና በጓደኝነት አንድ ላይ በመሰባሰብ እና በመቃወም በጓደኝነት መተባበርን እና መደጋገፍን መፍጠር። እርስ በእርስ በመድገጋገፍ የተለመደውን በመቃወም፣ በግል እና በጋ ራ ሃፍረትን በመቃወም እና ሀዘንን እንደራስ በመጋራት፣ የኩዊር ማንነትን በዚህ በማይለወጠው የጥቃት ስርዓት ውስጥ መኖርና ማለፍን በመረዳዳት ማሰስ።

**Fikir Woldekidan**
Personally Queer friendships changed my life.
All the loneliness , why am I the way I am , why can't I be normal goes away because now I have people to share it with. queer friendships are a safe space where we could question & share all the heteronormative practices we ended up internalizing.
It's just beka you give hope to each other and honestly that means the world to me , all the darkness just goes away.
You don't have to force your self to be something you are not anymore because you're not alone

ፍቅር ወልደኪዳን

በግሌ ኩዊር ጓደኝነት ህይወቴን ቀይሮታል።
ያ ሁሉ ብቸኝነት፣ እንዲህ የሆንኩት ለምንድነው ፣ ለምን ኖርማል አልሆንም የሚለው ሁሉ ይጠፋል ምክንያቱም አሁን የማጋራቸውና የማካፍላቸው ሰዎች አሉኝ። የኩዊር ጓደኝነቶች የደህንነት ቦታ ናቸው፣ በውስጣችን የያዝነውን እና የለመድውን የተቃራኒ ፃታ አፍቃሪያንን ብቻ ልክ እና የበላይ የሚለውን ሃሳብ የምንጠይቀበት ነው። በቃ ተስፋ መሰጣጣት ነው ፤ እውነት ያ ለኔ አለም ነው፣ ጨለማው ሁሉ ይገፈፋል። ያልሆነውን ለመሆን ራሳችንን ማስገደድ አይኖርብንም ምክንያቱም ብቻችንን አይደለንም።

**JuJu JuJu**
For me queer friendships have been a safe space. I always felt lighter and at ease after spending time with queer siblings who share similar ideals and accept me for me. Sometimes, I think of these friendships as therapy. Sharing the ups and downs of being a queer Ethiopian with my friends makes me feel seen and I'm not alone in the battlefield. 💖

ጁጁ ጁጁ

ለኔ የኩዊር ጓደኝነት የደህንነት ቦታ ሆኖልኛል። የኔን አይነት ተመሳሳይ ሃሳብ የሚጋሩ እና እኔን በእኔነቴ ከሚቀበሉኝ የኩዊር ወገኖቼ ጋር ሳሳልፍ ሁሌም ቅልል ያለ ስሜት ነው የሚሰማኝ። አንዳንዴም እነዚህን ጓደኝነቶች እንደ ምክር አገልግሎት እና ህክምና ነው የማያቸው። ኩዊር ኢትዮጵያዊ የመሆንን ውጣውረድ ለጓደኞቼ ሳካፍል እንደታየሁ እና እንደተሰማሁ አይነት ነው ስሜቱ፤ በጦርሜዳውም ብቻዬን እንዳልሆንኩ።